# - 7 -

# የኑብያና የአቢሲኒያ አብያተ ክርስቲያን ከ1000-1600 ዓ.ም.

ምዕራፍ አምስት ውስጥ የተመለከትነው፥ ቤተ ክርስቲያን በኑብያና በአቢሲኒያ እንዴት እንደተመሠረተችና በእስልምና መነሻ ወቅት፥ ከዚያም በኋላ እንዴት እንዳደገች ነው። እነዚህ አብያተ ክርስቲያን ከ700-1300 ዓ.ም. ስለነበሩበት ሁኔታ ብዙ እንደማናውቅ ምዕራፍ አምስት መጨረሻ ላይ አስገንዝበናል፤ ቢሆንም ባለፉት የተወሰኑ ዓመታት ምን እንደተፈጸመ የሚጠቁሙ አንዳንድ መረጃዎች አሉ።

## ኑብያ

ግብፅ በ641 ዓ.ም. በሙስሊሞች ከተወረረች በኋላ፥ በደቡብ ግብፅና በኑብያ መካከል ድንበር ተከለለ። በ650 ዓ.ም. አካባቢ በግብፅና በዶንጎላ ኑብያውያን መካከል የተፈረመ ስምምነት ነበር። በዚህ ስምምነት መሠረት፥ ኑብያውያን የግብፅ የድንበር ከተሞችን መዝረፋቸውን ካቆሙ፥ ዓረቦች ደግሞ ኑብያውያንን ላይተናኮሏቸው ተዋዋሉ። ይህ ስምምነት ለስድስት መቶ ዓመታት ተግባራዊ ሆኖ ቆይቷል። በእነዚህ ዓመታት ክርስትና የኑብያውያን እምነት ነበር።

በ1000 ዓ.ም. አካባቢ ኑብያውያን በሙስሊም ወራሪዎች ይጠቁ ጀመር። ከዚህ ጊዜ በፊት አልፎ አልፎ ግጭቶች ቢኖሩም ከ1000 ዓ.ም. በኋላ ግን እያየሉ መጡ። "በክርስቲያን ኑብያውያን ላይ ከካይሮ ራቅ ባሉት አካባቢዎች በሚኖሩት እስላም ገዢዎች ከሚደርስባቸው ይልቅ ከዘላን የዓረብ ነገዶች የሚሰነዘርባቸው ማስፈራራት የከፋ ሆነ። እነዚህ ዘላኖች በጊዜው የነበረው አስተዳደር በሚገባ የማይቆጣጠራቸው ስለነበሩ ቀስ በቀስ ወደ ላይኛው ግብፅ ዘለቁ። በመጨረሻም የኑብያ መከላከያ ኃይል በተዳከመ መጠን፥ ካታራክት ወደተባለው ክልልና ከዚያም አልፈው ገቡ።" ስለዚህ በ1000 ዓ.ም. ሰሜን ኑብያ ውስጥ የነበሩ አብዛኞዎቹ ሰዎች ከዘላን ዓረቦች ጋር በነበራቸው ግንኙነት የተነሣ ሰለሙ።

በ1000 ዓ.ም. በኑብያ ሁለት ዋና ዋና መንግሥታት ነበሩ። በስተሰሜን ከግብፅ ወሰን እንስቶ መርዌ እስከተባለው ደቡብ ወሰን ድረስ የተዘረጋና ማኩራ እየተባለ ይጠራ የነበረ መንግሥት ሲኖር፥ ዋና ከተማውም ዶንጎላ ይባል ነበር። ሌላው መንግሥት ከማኩራ ደቡብ የሚገኘውና አልዋ በመባል የሚታወቀው ሆኖ ዋና ከተማው ሶባ ይባል ነበር። "ሶባ ታላላቅ ገዳማት፥ በወርቅ የከበሩ አብያተ ክርስቲያንና ለነዚህ

የተሟላ ገጽታ የሰጧቸው የአትክልት ስፍራዎች ያሏት ውብ ከተማ እንደነበረች ኢብን ሳሊም በተባለ ሰው ተገልጧል። የአገሪቱ ሕዝቦች በእስክንድርያው ፓትሪያርክ የተሾሙ ጳጳሳት የነበሯቸው ክርስቲያኖች ሲሆኑ፥ ወደ ራሳቸው ቋንቋ በተረጎሟቸው የግሪክ ሥነ-ጽሑፎች ይጠቀሙ ነበር።"

የኑብያ አብያተ ክርስቲያን በአሥራ ሁለተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጠንክረው የሚቆዩ ይመስሉ ነበር። ማኩራ ውስጥ ብዙ አብያተ ክርስቲያንና ገዳማት ነበሩ። አልዋ ውስጥ ደግሞ ከ400 በላይ አብያተ ክርስቲያን እንደነበሩ ይነገራል።

በኑብያ ክርስትና ላይ የመጀመሪያው የከፋ ፍርሃት የተከሰተው በ1275 ዓ.ም. ነው። የማኩራ ዋና ከተማ ዶንጎላ በግብፃውያን የተያዘችው ያን ጊዜ ነበር። ግብፃውያን እነርሱን የሚደግፍ ንጉሥ ዙፋኑ ላይ እንዲቀመጥ አደረጉ። ያ ጥገኛ የሆነ የመጀመሪያ ንጉሥ ምናልባት ክርስቲያን ሳይሆን አይቀርም። "የመጀመሪያው ንጉሥ ሙስሊም ስለመሆኑ እስከ 1316 ዓ.ም. ድረስ የሰማነው ነገር የለም። ሕዝቡ ያኔም ክርስቲያን ነበር።" የማኩራን መንግሥት በእጁ ያደረገው እስልምና በቀላሉ በረታ።

ክርስቲያኖች በአሥራ አምስተኛው ክፍለ ዘመን የመጨረሻ ዓመታት (በ1480 ዓ.ም.) አልዋ ይገኝ የነበረው መንግሥት አባላት በሆኑትና ፈንግ በተሰኙት ሕዝቦች ይፈተኑ ጀመር። የፈንግ ሕዝቦች በ1504 ዓ.ም. ሶባን በወረራ ይዘው አዲስ ዋና ከተማ መገንባት ጀምረው ነበር።

የኑብያ ክርስቲያኖች ከ1275-1600 ዓ.ም. ባለው ጊዜ፥ በሙስሊሞች እሥራት ወይም በሞት የተሰደዱ አይመስልም። ይልቁንም ሕዝቡ ዓመታትና ዘመናት ባለፉ ቁጥር፥ ከክርስትና ወደ እስልምና የተለወጠ ነው የሚመስለው። በኑብያና በኢትዮጵያ ክርስቲያኖች መካከል ብዙ ግንኙነት እንዳልነበረ ሊታወስ ይገባል። ከዚሁ ጋር በኑብያ ክርስቲያኖች ዙሪያ ያሉት ሁሉ አረማውያን ወይም ሙስሊሞች ነበሩ። ኑብያውያን ከግብፅ ኮፕቲክ ክርስቲያኖች ጋር አንዳንድ ግንኙነቶች የነበራቸው ቢሆንም፥ እምነታቸውን ጠብቀው ለማቆየት ከውጭው ዓለም የሚያስፈልጋቸውን እውነተኛ እርዳታና ማበረታቻ አላገኙም። ስለሆነም ከክርስትና ወደ እስልምና የሚደረገው ለውጥ አዝጋሚ ቢሆንም፥ በአሥራ ሰባተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የኑብያ ቤተ ክርስቲያን የሞተች ትመስል ነበር።

የኑብያ ቤተ ክርስቲያን አሁን ባትኖርም፥ በአፍሪካ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ተገቢ ስፍራ ልንሰጣት ይገባል። ከቀረው

ክርስቲያናዊ ዓለም ጋር እጅግ አነስተኛ ግንኙነት በነበረበት ጊዜ ቤተ ክርስቲያኒቱ ከ1000 ዓመታት በላይ ሕልውናዋን ጠብቃ ኖራለች። ምንም እንኳ በሙስሊም ሕዝብ የተከበበችና ከፍተኛ ተጽዕኖ የነበረባት ብትሆን፥ ጠንካራ መሠረት ስለነበራት፥ ለብዙ ዘመናት ልትጸና ችላለች።

## አቢሲኒያ

ኑብያ ውስጥ የነበሩት የክርስቲያን መንግሥታት ከ600-1200 ዓ.ም. በነበረው ጊዜ በዘላን ግብፃውያን ሙስሊሞች ፈተና ገጥሚቸው ነበር። አቢሲኒያ ግን በዚህ ጊዜ የሙስሊሞች ጉዳይ እምብዛም አላስጨነቃትም። “ለመካከለኛው ዘመኒቱ ኢትዮጵያ እውነተኛው አደጋ የመጣባት ከሰሜን ሙስሊሞች ሳይሆን፥ በደቡብ ከሚገኙት አረማውያን ነበር። ስለዚህ ጉዳይ የምናውቀው ዝርዝር ነገር የለም። አንድ ከጥፋት የተረፈ ደብዳቤ አለ። ይሄውም በአሥረኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጨረሻ ላይ አንድ ኢትዮጵያዊ ንጉሥ፥ ለኑብያው ንጉሥ ጆርጅ የጻፈው ሲሆን፥ ጎረቤቱ በሆነ አረማዊ መንግሥት ተወሮ በመጥፋት ላይ ስለነበረው መንግሥት አሳዛኝ ታሪክና ጉዳት የሚገልጥ ነው።” ኢትዮጵያውያን መንግሥታቸውን እንደገና ለመገንባት ለሁለት ምዕተ ዓመታት ተኩል ታገሉ። ይህ ተግባር እጅግ ከባድ ነበር። የንጉሡ ጥረት ባይሳካ ኖሮ ምናልባት ክርስትና ከብዙ ዓመታት በፊት ከኢትዮጵያ ይጠፋ ነበር።

ነገሥታቱ ፖለቲካዊ መንግሥት ለመገንባት በሚጥሩበት ጊዜ፥ የኮፕቲክ መነኮሳትና ባሕታውያን ደግሞ በሕዝቡ መካከል ቤተ ክርስቲያን ያንጹ ነበር። የዛጉዌ ሥርወ መንግሥት ነገሥታት የኢትዮጵያ ኮፕቲክ ክርስቲያኖች እስከ ዛሬ የሚጠቀሙባቸውን ከድንጋይ የተፈለፈሉ የሮሃ አብያተ ክርስቲያን ያነጹት ያኔ ነው።

ይህ መንግሥት በ1270 ዓ.ም. ወሰኑን እያስፋፋ የአማራ፥ ላስታ፥ ጎጃምና ዳሞት ጠቅላይ ግዛቶችን ከክልሉ ቀላቀለ። መንግሥቱ እጅግ እየሰፋ ስለሄደ ማዕከሉን ቀድሞ ከነበረበት ከሰሜኑ የትግራይ ጠቅላይ ግዛት ወደ አማራው ክልል አዛወረ።

በዚህ ሁኔታ ኢትዮጵያውያን ከ980-1270 ዓ.ም. በነበረው ጊዜ በስተደቡብ የሚገኙትን አረማዊ መንግሥታት ድል በማድረጉ ተግባር ተጠምደው ሳለ፥ ሙስሊሞች በቀይ ባሕር ዳርቻ ይሰፍሩ ጀመር። ስለዚህ በአሥራ ሦስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጨረሻ አካባቢ ኢትዮጵያውያን በሙስሊሞች አማካይነት ከባሕሩ በመለያየት ላይ መሆናቸውን ተገነዘቡ። በ1270 ዓ.ም. አዲስ ንጉሥና አዲስ ሥርወ መንግሥት ተመሠረተ። ይህ አዲስ ንጉሥ ከሙስሊሞች ጋር ውጊያ ስለጀመረ፥ ከእርሱ በኋላ የተነሡት




ነገሥታት በ14ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ሙስሊሞችን ተቋቁመዋቸው ነበር። ይህ አዲስ ንጉሥ ኢትዮጵያውያን የክርስትና መሪዎችን ስለ ክርስትናና ስለ ቤተ ክርስቲያኖቻቸው ይበልጥ እንዲያነቡና እንዲጽፉ አበረታታቸው። እንደገና ኢትዮጵያውያን ለጽሑፎቻቸው የራሳቸውን ግዕዝኛ መጠቀም ጀመሩ። በዚህ መንገድ ማንበብና መጽሐፍ የተማሩት ሰዎች ቅዱሳት መጻሕፍትንና በቤተ ክርስቲያን የተጻፉ መጻሕፍቶችን ይረዱ ነበር።

በአሥራ አምስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ ላይ በጠረፉ የነበሩት ሙስሊሞች ኢትዮጵያን ይፈታተኗት ጀመር። ዘርዓ ያዕቆብ በ1434 ዓ.ም. ነገሠ። ይህ ንጉሥ ሙስሊሞች ኃይላቸውን በዚህ አኳኋን ማጠናከራቸውን ከቀጠሉ የአቢሲኒያን ክርስቲያኖች በሙሉ እንደሚያጠፏቸው ተገነዘበ። መንግሥቱን የሚያድንበትም ብቸኛ መንገድ የአውሮፓ ክርስቲያኖችን እርዳታ በመጠየቅ መሆኑን ስለተረዳ ይህንኑ ለማድረግ ወሰነ። በዚሁ መሠረት እርዳታ በመጠየቅ ወደ ሮማው ሊቀ ጳጳሳት ደብዳቤ ላከ። ያኔ ፖርቱጋሎች ወደ ህንድ የሚወስደውን የባሕር

መንገድ ገና ስላላገኙት የሮማው ሊቀ ጳጳስ ንጉሥ ዘርዓ ያዕቆብን የሚረዳበት ቀላል መንገድ አልነበረውም። ያም ሆኖ ንጉሡ ሙስሊሞች ወደፊት እንዳይገፉ ገትቷቸው ነበር።

ኢትዮጵያውያን ከፉ ጊዜ የገጠማቸው በልብነ ድንግል ዘመነ መንግሥት (1508-1540 ዓ.ም.) ነው። በአሥራ ስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ አንድ ሶማሊያዊ የሙስሊሞች አለቃ ኢትዮጵያን ወረረ። ወራሪው በባሕሩ ዳርቻ ከነበሩ የዓረብ ነጋዴዎች ባገኘው የጦር መሣሪያ ኢትዮጵያውያንን ድል አደረገና አብዛኛውን የሰሜን ኢትዮጵያ ክፍል፥ አክሱምን ሳይቀር ያዘ። ቤቶችንና አብያተ ክርስቲያንን አቃጠለ። "...ይህ ወረራ ከፍተኛ ውጤት ማግኘቱንና በወረራው ምክንያት ከአሥር ዘጠኙ ሰው ወደ እስልምና የተለወጠ መሆኑን የአቢሲኒያ ዜና መዋዕሎች ይናገራሉ።" አያሌ ሰዎች ወደ እስልምና ቢለወጡም፥ በእምነታቸው የጸኑና አፄ ልብነ ድንግል ለአሥራ አምስት ዓመት ባደረገው ውጊያ የረዱት ብዙ ኢትዮጵያውያንም ነበሩ።

አፄ ልብነ ድንግል ያለበቂ የጦር መሣሪያ ሶማሊያዊውን የኀሳ መሪ በቀላሉ ድል እንደማያደርገው በመገንዘብ ፖርቱጋሎችን እርዳታ ጠየቀ። መገናኛው አስቸጋሪ ከመሆኑና ጉዞውም አዝጋሚ ከመሆኑ የተነሣ 400ዎቹ የፖርቱጋል ወታደሮች ኢትዮጵያውያንን ለመርዳት የደረሱት በ1541 ዓ.ም. ነበር። ያኔ ንጉሥ ልብነ ድንግል ሞቷል። ነገር ግን ዙፋኑን ከእርሱ የተረከበው ንጉሥ ገላውዴዎስ ከሙስሊሞች ጋር ውጊያ ቀጥሎ ነበር። በ1543 ዓ.ም. የሶማሊው ወራሪ እስኪገደልና የቀረው የአቢሲኒያ ክፍል በክርስቲያኖች እጅ እስኪገባ ኢትዮጵያውያንና ፖርቱጋሎች ከሙስሊሞች ጋር ብዙ ጦርነቶች አድርገዋል። የኢትዮጵያ ኮፕቲክ ቤተ ክርስቲያን በተፈለገ ጊዜ በደረሰው የፖርቱጋሎች እርዳታ በሙስሊሞች ከመደምሰስ ዳነች።

አሥራ ስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ለአፍሪካ የወንጌል ሥራ አዲስ ሙከራ የተጀመረበት ጊዜ ስለሆነ፥ በአፍሪካ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ እጅግ ጠቃሚ የነበረውን ጊዜ ወደ ማጠቃለሉ ተቃርበናል። አሥራ ስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ላይ ቆም ብለን የአፍሪካን የ1500 ዓመታት የክርስትና ታሪክ ወደ ኋላ ስንመለከት፥ ክፍለ አህጉሪቱ ውስጥ አብያተ ክርስቲያን እንደነበሩ እንገነዘባለን! የግብፅ ኮፕቲክ ቤተ ክርስቲያን፥ በሙስሊሞች የተከበበች ብትሆንም፥ በአብዛኛው የግብፅ ክፍል በመሥራት ላይ ነበረች። የአቢሲኒያ ኮፕቲክ ቤተ ክርስቲያን ደግሞ የእስልምናን የመስፋፋት ወረራ ተቋቁማ ታላቅ በሆነችው ምድር ክርስትናን ለማቆየት ችላለች።

ይህም ቢሆን እነዚህ ሁለት ብሔራዊ አብያተ ክርስቲያን በአሥራ ስድስተኛው ክፍለ ዘመን ያደረጉት ነገር ቢኖር ሕዝቦቻቸውን መከላከልና መጠበቅ ነበር። በምድራቸው እምነታቸውን በመከላከል ተግባር ተወጥረው ስለነበር፥ ወንጌል ወዳልደረሰባቸው የአፍሪካ ክፍሎች ለመንዛ ፍላጎቱ ቢኖራቸውም፥ አልቻሉም። በአህጉሪቱ ሌሎች ክፍሎች ወንጌልን ለማዳረስና ክርስትናን ለማስፋፋት እንደ ፍሬምናጦስና ሎንጂነስ ያሉ አዳዲስ ሚስዮናውያን አስፈልገው ነበር። ይህ ሆነና በአሥራ ስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በአዲስ አቅጣጫ ክርስትና ወደ አፍሪካ ይመጣ ጀመር። በአፍሪካ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ይህ እድገት እንዴት እንደተከናወነ ከጥቂት ገጾች በኋላ እንመለከታለን።

## ጥያቄዎች

1. የኑብያ ሁለት ክርስቲያናዊ መንግሥታት እነማን ነበሩ?
2. የግብፅ ሙስሊሞች የማኩራን ዋና ከተማ የያዙት መቼ ነው?
3. ሙስሊሞች የኢትዮጵያን ንጉሥ ያጠቁት በየትኛው አቅጣጫ ነበር?
4. አፄ ያዕቆብ እርዳታ የጠየቀው ከማን ነበር?
5. በአሥራ ስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ፖርቱጋል የኢትዮጵያን ንጉሥ የረዳችው እንዴት ነበር?

- 8 -

# ከቀድሞዎቹ የአፍሪካ አብያተ ክርስቲያን የወረስናቸው ቅርሶች

በአፍሪካ በ1500 ዓ.ም. አካባቢ የነበረውን ፖለቲካዊና ሃይማኖታዊ ሁኔታ ከመመልከታችን በፊት ሁኔታው፥ ለእኛና ለቤተ ክርስቲያናችን የሚኖረውን ታሪካዊ ጉዳይ ማሰብ ብልህነት ሳይሆን አይቀርም። ዛሬ በአፍሪካ የሚገኙት አብያተ ክርስቲያን፥ ጥንት ከነበረችው የአፍሪካ ቤተ ክርስቲያን ብዙ ነገሮች የተቀበሉ መሆናቸውን በመግቢያው ገልጫለሁ። የቀድሞዎቹ አፍሪካውያን ክርስቲያኖች ባለ ዕዳ ስለሆንን ከእነርሱ የተቀበልናቸውን ነገሮች ጠንቅቀን ልናውቅ ይገባል። ጥቅም ካገኘንባቸው ከነዚህ ቅርሶች ሌላ፥ ልንማራቸው የሚገቡ አንዳንድ ትምህርቶችም አሉ። የቀድሞዎቹ ክርስቲያኖች ብንከተላቸው መልካም የሆኑ ብዙ ምሳሌዎች ትተውልናል። ብዙ ጊዜም "ከስሕተታችን መማር አለብን" ተብሎ በተደጋጋሚ ተነግሯል። ስለዚህ በቀድሞይቱ የአፍሪካ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተሠራውን ስሕተት፥ ዛሬም በቤተ ክርስቲያናችን እንዳንደግም ንቁ መሆን አለብን።

ለዘመናችን ክርስትና እጅግ ጠቃሚው ነገር ለክርስቶስ ታማኞች የመሆናችን ጉዳይ ነው። ዛሬ በአፍሪካ ባለች ቤተ ክርስቲያን ለኢየሱስ ክርስቶስ ትምህርት በእውነት መቆም አስፈላጊ እንደሆነ እናምናለን። ኢየሱስ ስለ ደኅንነትና ዘላለማዊ ሕይወት ባስተማራቸው ትምህርቶች ላይ ምንም ዓይነት ድርድር ሊኖር እንደማይችልም እናምናለን። ይህን ስናደርግ በሁለተኛውና በሦስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን፥ "አፍሪካና" ግብፅ ውስጥ የነበሩ ክርስቲያኖችን ዱካ መከተላችን ነው። ብዙዎች በክርስቶስ በማመናቸውና በእምነታቸው በመጽናታቸው፥ በሮም መንግሥት መገደላቸውን አንብበናል። እነዚህ የጥንት አፍሪካውያን ክርስቲያኖች፥ በዓለም ላይ ለእነርሱ ጠቃሚ የሆነ ዋናና ብቸኛ ነገር ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሆነ ተገንዝበው ነበር። ኢየሱስ ከእኛ የሚፈልገው፥ ሙሉ ታማኝነትን እንደሆነም ተረድተዋል። "በሰው ፊትም የሚክደኝን ሁሉ እኔ ደግሞ በሰማያት ባለው በአባቴ ፊት እክደዋለሁ" (ማቴ. 10፥33)። የጥንት አፍሪካውያን ክርስቲያኖች ደካሞች ወይም፤ ባመኑት ነገር ለመቆም የሚፈሩ አልነበሩም። ቤተ ክርስቲያናችን ለኢየሱስ ክርስቶስ ስትቆም ይህን መልካም ምሳሌነት በመከተል ላይ ናት ለማለት እንችላለን።

የጥንቷ አፍሪካዊት ቤተ ክርስቲያን ሌላ ትኩረት፥ የወንጌል ሥራና በሚስዮናውያን ሌሎችን መድረስ ነበር። "አፍሪካና" ግብፅ ውስጥ የነበሩ የጥንት ክርስቲያኖች እምነታቸውን ለሌሎች መንገር ይፈልጉ

እንደነበር በጥናታችን ተረድተናል። ከ312 ዓ.ም. በፊት በመስከሩ፥ ወይም ሰዎችን ወደ ጌታ ለመምራት በፈለጉ ጊዜ ለስደት ተዳርገዋል። ቢሆንም ስደቱ ለወንጌል ሥራ የነበራቸውን ፍላጎት አልገታውም። የወንጌል ሥራ ቅድሚያ አግኝቶ ባይሆን ኖሮ፥ ቤተ ክርስቲያን እስከዛሬ በፍጥነት ለማደግም ሆነ ለመስፋፋት ያዳግታት እንደነበር ግልጥ ነው። እድገቷ ሊሰፋ የቻለው አባላቷ በአካባቢያቸው ወዳሉት መንደሮች በመሰማራት መልካሙን የምሥራች በማሰራጨታቸው ነው። ዛሬም አፍሪካ ውስጥ ባለን አብያተ ክርስቲያን ዘንድ ያለው ፍላጎት፥ ሰዎች ሁሉ ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ የማዳን እውቀት ሲመጡ ማየት ነው። የአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናችን ምዕመናን በዙሪያቸው ላሉ ሰዎች የወንጌሉን የምሥራች በሚነግሩበት ጊዜ፥ የአፍሪካ ምዕመናን ከብዙ መቶ ዓመታት በፊት ያደርጉት የነበረውን አርአያ ተቀብለው መቀጠላቸው ነው።

ስለዚህ በምዕራፍ ሦስት በተመለከትነው መሠረት እንደ ተርቱሊያን፥ አውግስጢኖስና ሌሎች የአፍሪካ ቤተ ክርስቲያን አባቶች ያደረጉት ከፍተኛ አስተዋጽኦ የዛሬይቱን የአፍሪካ ቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ ባለ ዕዳ ያደርጓታል። ስለ ሥላሴ በግልጥ የጻፈ፥ እንዲያውም ስለ እግዚአብሔር ያለንን መረዳት ለመግለጥ "ሥላሴ" የሚለውን ቃል የሰጠን ተርቱሊያን ነው። እንዲሁም ለክርስትና ትምህርተ-መለኮት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረገው አውግስጢኖስ እንደነበር ተረድተናል። ዞር ብለን በታሪክ ስንመለከት፥ እነዚያ አፍሪካውያን ክርስቲያኖች ያደረጉት አስተዋጽኦ ባይኖር ኖሮ፥ የዛሬይቱ ቤተ ክርስቲያናችን አሁን ያለችበት ሁኔታ የተለየ ይሆን እንደነበር እንረዳለን። እነዚያ የጥንት አፍሪካውያን ክርስቲያኖች ለቤተ ክርስቲያናችን እጅግ የላቀ ቅርስ አበርክተውላታል። ቅርሱ የአፍሪካ ብቻ ሳይሆን፥ በዓለም ዙሪያ ያለች ቤተ ክርስቲያንም ነው።

ከአፍሪካ ቤተ ክርስቲያን የመጀመሪያዎቹ ዓመታት የምንቀስማቸው ሌሎች ትምህርቶችም አሉ። በጥናታችን በግልጥ የተመለከተው ዋና ጉዳይ፥ ምናልባት ቤተ ክርስቲያንን እጅግ ያዳከማት የመከፋፈልና የግለሰቦች መጋጨት ነው። ለጥንቷ ቤተ ክርስቲያን መከፋፈል አብዛኞዎቹ መንስዔዎች፥ ቀስ በቀስ ወደ ቤተ ክርስቲያን የዘለቁ የሐሰት ትምህርቶች እንደነበሩ ልብ ብለናል። የመከፋፈሎቹና የሐሰት ትምህርቶቹ ውጤት በአንዳንድ ስፍራዎች የቤተ ክርስቲያን ፈጥኖ መጥፋት እንደነበር ተገንዝበናል። ለአብነት ያህልም አርዮሳዊነት እና ዳናተሳዊነት የ"አፍሪካ"ን ቤተ ክርስቲያን እንዴት እንደከፋፈሏት ተመልክተናል። እውነተኛው ክርስትና እንደገና ወደ ስፍራው ከገባ በኋላም ቢሆን ቤተ ክርስቲያን በጣም ጠንካራ አልነበረችም። ከዚያም በ697 ዓ.ም. እስልምና በመጣ ጊዜ ቤተ ክርስቲያን ጭራሽ የመነመነች መሰለች። ከዚህ

የምንቀስመው ትምህርት ግልጥ ነው። ዛሬም በቤተ ክርስቲያናችን ወደ ምዕመናን ሾልከው የሚገቡ የሐሰት ትምህርቶችን በንቃት መጠበቅ አለብን። ለወንጌልና ለመሠረታዊ የእምነት ትምህርቶቻችንም ጸንተን ልንቆም ይገባል። በግለሰቦች መካከል በሚፈጠሩ ችግሮች ሳቢያ የሚነሡ የቤተ ክርስቲያን መከፋፈሎችንም ማስወገድ አለብን። ቤተ ክርስቲያን እድገቷ ሳይገታ ትቀጥል ዘንድ መጋቢዎችና የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሁሉ በአንድነትና በስምምነት መኖርን መማር አለባቸው። "ወንድሞች በኅብረት ቢቀመጡ እነሆ መልካም ነው እነሆም ያማረ ነው" (መዝ. 133፡1)።

ሌላው ጠቃሚ ትምህርት፥ የቤተ ክርስቲያን አባላት ቅዱሳት መጻሕፍትን ይሰሙና ይማሩ ዘንድ መጽሐፍ ቅዱስ በሕዝቡ ቋንቋ መተርጎም ያለበት መሆኑ ነው። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱስን ወደ ግዕዝ የተረጎመችበትንና ሌሎች ክርስቲያናዊ መጻሕፍትንም በሀገርኛ ቋንቋዎች ያዘጋጀችበትን ሁኔታ ተመልክተናል። ሲ. ፒ. ግሩቭስ የተባለ ጸሐፊ ስለ ኢትዮጵያ እንዲህ ብሏል፦ "የሕዝቡ ቋንቋ አጠቃቀም፥ እንደ ከባድ ማዕበል ባሉ የውጥረት ጊዜያት እንኳን ክርስትናን ከመጠበቁ ጋር የተያያዘ ነው።" ይህ የሚያመለክተን፥ በጉባኤ መካከል መጽሐፍ ቅዱስ እንዲኖር የማድረጉን ጥቅም ነው። የቤተ ክርስቲያን መጋቢያንና፥ ምዕመናን ቅዱሳት መጻሕፍትን የመማር ፍላጎት እንዲያድርባቸውና መጽሐፍ ቅዱስን እንዲያነቡ መበረታታት አለባቸው። እንዲያ ከሆነ፥ ለቤተ ክርስቲያን አስቸጋሪ የሆነ ጊዜ ቢመጣ ሕዝቡ ለክርስቶስ ጸንቶ ለመቆም የተሻለ ችሎታ ይኖረዋል።

ከታሪክ የምናገኘው ሦስተኛ ትምህርት፥ ክርስትና በተግባር ላይ ሲውል፥ ከአንድ ሕዝብ ብሔራዊ ባሕል ጋር የሚዋሀድበት ሁኔታ ጥንቃቄ የሚያሻው መሆኑን ነው። ክርስትና መጀመሪያ ወደ ግብፅ በገባ ጊዜ ወንጌልን ከባሕላዊ ሃይማኖታቸው ጋር ለመደባለቅ የሞከሩ አያሌ ግብፃውያን ነበሩ። ከሁለተኛው እስከ አምስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ግብፅ ውስጥ የነበረችውን ቤተ ክርስቲያን አስመልክቶ ግሩቭስ የተባለው ሰው ሲጽፍ፦ "የሞቱ ሰዎችን በድን በተለየ ንጥረ ነገር አድርቆና በልዩ ልብስ ጠቅሎ የማቆየት ተግባር (Mummification) በግብፅ ክርስቲያኖች ዘንድ እስከ አምስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ድረስ ቀጥሎ ነበር። ለሞቱ ሰዎች ምግብ የማቅረብ ሥርዓት በክርስቲያኖች ዘንድ የነበረ ይመስላል። ይህ ድርጊት ለሙታን አስማታዊ ምግብ ማቅረብ ያስፈልጋል የሚለው የግብፃውያን አሳብ እንሠራርቶ እንደነበር ያመለክታል" ብሏል። የኋላ ኋላ ግን ድርጊቱን ክርስቲያኖች ተዉት። ይህ እስኪሆን ድረስ ቤተ ክርስቲያን ጠንካራ ምስክርነት ለመስጠት አልቻለችም ነበር። ይህ ድርጊት የዛሬይቱ

የአፍሪካ ቤተ ክርስቲያን ባሕላዊ ሃይማኖትን ከክርስትና ጋር በመቀላቀል እውነተኛና ምሉዕ የሆነውን ክርስትና ይበልጥ የሚታመን ያደረጉ የሚመስላቸውን ሰዎች ከመካከሏ በማስወገዱ ረገድ እንደ ማስጠንቀቂያ ያገለግላል። እምነታችንን ከምንገልጥባቸው መንገዶች ጋር የሚሄዱ አንዳንድ መልካም የአፍሪካ ባሕሎች ቢኖሩም፥ የሚቀርብልንን ነገር ሁሉ እንዳንቀበል መጠንቀቅ ይኖርብናል። ያለዚያ ውጤቱ በሁለተኛውና በሦስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በግብፅ ቤተ ክርስቲያን እንደሆነው አስማትና ጥንቆላን ከአንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ አሳቦች ጋር ቀላቅላ የያዘች ደካማ ቤተ ክርስቲያንን ማፍራት ይሆናል።

በመጨረሻም የቤተ ክርስቲያን መጋቢዎች ቤተ ክርስቲያንን የመገንባትና ሕልውናዋን ጠብቃ እንድትኖር የማድረግ ጠቃሚ ድርሻ እንዳላቸው ማስታወስ ይገባቸዋል። ብዙ ሰዎች የቤተ ክርስቲያን እድገት፥ የታላላቅ የወንጌል ስብሰባዎች፥ የክርስቲያናዊ ሥነ-ጽሑፎች ወይም የክርስቲያናዊ ፊልሞች. . . ወዘተ. ውጤት ነው ብለው ያስባሉ። ብዙ ጊዜ ግን እንዲያ አይደለም። ቤተ ክርስቲያን ከሁሉ የላቀ እርዳታ የምታገኘው ከታማኝ መጋቢዎችና ሽማግሌዎች ነው። መንፈሳዊ ያልሆነ አንድ የታሪክ ሰው ስለ ኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ያደረገውን ጥናት እንዲህ በማለት ገልጧል፡- "ክርስትና ድል ያደረገው ቁጭ ብሎ በትምህርት የተገኘን እምነት በማወጅ ሳይሆን፥ በቅድስናቸውና ዓለምን በመካድ ባሳዩት አርአያነት በምዕመናኑ ላይ ሃይማኖታዊ ተፅዕኖ ባሳደሩ መነኩሳትና መናኝ ባሕታውያን ነው።"

በዚህ ጸሐፊ አባባል መሠረት የኢትዮጵያ ኮፕቲክ ቤተ ክርስቲያን ያደገችው፥ በጥቂት ታላላቅ ሰባኪያን ቃል ሳይሆን፥ ትክክለኛና ንጹሕ ሕይወት ይኖሩ በነበሩ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን መጋብያን (መነኩሳት) ነበር። የእነዚህ ሰዎች ፍላጎት ሀብት ወይም ዝና ማግኘት ሳይሆን፥ መልካም ክርስቲያናዊ ምስክርነት ብቻ ነበር። ይህ፥ መጋቢ ለመሆን የሚፈልጉ ሰዎች ሁሉ ሊማሩት የሚገባ ትምህርት መሆን አለበት። አገልጋዮች በዙሪያቸው በሚኖሩት ሰዎች ሕይወት ከፍተኛ በጎ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ የሚችሉት፥ በየእሁዱ አስደናቂ ስብከት እየሰበኩ በሳምንቱ ቀናት ደካማ ክርስቲያናዊ ሕይወት መኖራቸው ሳይሆን፥ በየዕለት ሕይወታቸውና ተግባራቸው ነው።

ከዚህ የታሪክ ክፍለ ጊዜ የምንቀስማቸው ሌሎች ብዙ ትምህርቶች አሉ። ሆኖም የቤተ ክርስቲያንን ታሪክ የማወቅን ጥቅም ለመረዳት ያህል እነዚህ ይበቁናል። ትምህርቶቹ ቤተ ክርስቲያናችን ንጹሕና ጠንካራ መሆኗን የማረጋገጥ ፍላጎት እንዲያድርብን ሊያደርጉ ይገባል።

# - 9 -

# የአፍሪካ እድገት
# እስከ 1500 ዓ.ም.

በአሥራ ስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ አፍሪካ የተለያዩ ሁኔታዎች የሚታዩባት አህጉር ነበረች። ከተለያዩ ብዙ የዓለም ክፍሎች ጋር የንግድ ልውውጥ ያደርጉ የነበሩ የሙስሊሙ አፍሪካ ክፍል ታላላቅ ከተሞች በሰተሰሜን ነበሩ። በምዕራብ አፍሪካ እምብርት ደግሞ የአሥራ ሦስተኛ፥ የአሥራ አራተኛና የአሥራ አምስተኛ መቶዎቹን ክፍለ ዘመናት ታላላቅ ንጉሣዊ አገዛዞች የተከሉ መንግሥታት ነበሩ። በደቡብ አፍሪካ፥ አፍሪካውያን እንደ ዚምባብዌ ያሉ ትላልቅ ባለድንጋይ ሕንጻ ከተሞችን ገንብተው፥ ወደ ህንድና የዓረብ ምድር ለገበያ የሚላክ ወርቅ ሶፋላ ወደተባለ ስፍራ በማቅረብ ላይ ነበሩ። በምሥራቅ አፍሪካ የባሕር ዳርቻዎች ብዙ የንግድ ከተሞች ነበሩ። የዓረብ ነጋዴዎች ከመሀል አገሮች የዝሆን ጥርስ እየገዙ በመርከብ ወደ ምሥራቅ ያጓጉዙ ነበር። ወደ መካከል ገባ ብሎ ደግሞ፥ እውቀታቸው እርሻና የብረት ሥራ ብቻ የሆነ ነገዶች ኖረዋል። ከአንዳንድ የአፍሪካ ክፍሎች ጋር ሲነጻጸሩ፥ እነዚህ ነገዶች የሚገለገሉበት ጽሑፍ ወይም ፊደል አልነበራቸውም። የሙስሊምም ሆነ የክርስቲያን ሚስዮናውያን ስላልደረሱባቸው፥ የራሳቸውን ባሕላዊ ሃይማኖት ነበር የሚያመልኩት። እንዲህ ያሉ ታላላቅ ልዩነቶች የነበሯትን የዚያን ጊዜዋን አፍሪካ በጥቂት ቃላት መግለጡ ያዳግታል። ቢሆንም የቤተ ክርስቲያንን እድገትና ብልጽግና ለመገንዘብ፥ ያን ጊዜ አፍሪካ ስለነበረችበት ሁኔታ አንዳንድ ነገሮችን ልናውቅ ይገባል።

ከሰሜን ብንጀምር፥ በአጠቃላይ ከ800-1500 ዓ.ም. የነበረው ጊዜ "የሰሜን አፍሪካ ወርቃማ ዘመን" ሊባል ይችላል። የሰሜን አፍሪካ መንግሥታት ያኔ በዓለም ላይ ከሚገኙትና በጣም ከላቁት ጥቂት መንግሥታት መካከል የሚቆጠሩ ነበሩ። ነገር ግን ያ ብቃት ብዙ ችግር ይዞ ነበር የመጣው። የሰሜን አፍሪካ አገሮች በተለያዩ የሙስሊሞችና የበርበር ቡድኖች ያለማቋረጥ ይጠቁ ጀመር። እርግጥ ነው እስልምና ራሱም በ1000 ዓ.ም. ብዙ የተለያዩ ክፍፍሎች ደርሰውበት ነበር። እያንዳንዱ የሙስሊም ቡድን ሌሎቹ ቡድኖች የእርሱን የሃይማኖት አተረጓጎም እንዲከተሉ ለማስገደድ ሞክሯል።

ከ1000-1300 ዓ.ም. ድረስ በነበረው ጊዜ የተለያዩ የበርበር ሃይማኖታዊ ቡድኖች ሰሜን አፍሪካንና የምዕራብ አፍሪካ አንዳንድ ክፍሎችን አስተዳድረዋል። በ1300 ዓ.ም. ግን የበርበሮች የበላይነት




አበቃ። ውጤቱም የሰሜን አፍሪካ በ1500 ዓ.ም. በአራት ዋና ዋና ክፍሎች


የንግድ መንገድ
ከሰሜን/ምዕራብ አፍሪካ




የማሊ ንጉሣዊ ግዛት

አረማውያን ቁጥር ከሙስሊሞቹ እጅግ የላቀ ነበር። ማንሳ ሙሳ በ1337 ከሞተ በኋላ ግን የማሊ መንግሥት ይዳከም ጀመር። በ1500 ዓ.ም. ፈጽሞ ጠፋ።

የሌላ ታላቅ መንግሥት መነሣት የታየው የሶንግሃይ ሕዝብ በ1375 ዓ.ም. ከማሊ ተላቆ ነጻነቱን እንደገና ካገኘ በኋላ ነው። እነዚህ ሕዝቦች በናይጀር ወንዝ መካከለኛ ክፍል ጠንካራ መንግሥት መሠረቱ። በ1464 ሱኒ አሊ የተባለ ሰው የሶንግሃይ ንጉሠ ነገሥት ሆነና፥ መንግሥቱን ይበልጥ ያጠነክር ጀመር። በ1468 ዓ.ም. ናይጀር ውስጥ እጅግ ጠቃሚ የንግድ ከተማ የነበረችውንና ቲምቡክቱ የተባለችውን ስፍራ ያዘ። ቀጥሎ የያዛት ከተማ በወርቅና በኮላ ንግድ ጠቀሜታ ያላት ጄኔ ናት። አሊ የከተሜው ማኅበረሰብ ሃይማኖት ለነበረው እስልምና የፈየደው ነገር አልነበረም። የመቀለድ ያህል ያደረጋቸው ጸሎቶቹ እንደሚያሳዩት እስልምናን የሚመለከተው በፌዝ ነበር። ይህ ሰው በ1492 ዓ.ም. አካባቢ ሞተ።

ከእርሱ ሞት በኋላ በሶንግሃይ ላይ የነገሠው መሐመድ ቱሬ የተባለ ሰው ነበር። መንግሥቱን ከገነባበት፥ ካደራጀበትና ካጠናከረበት ሁኔታ ጋር በማዛመድ አንዳንድ ጊዜ ታላቁ አስኪያ በመባል ይጠራል። ግዛቱን በተገቢው መንገድ ለመምራት ያመቸው ዘንድ ማዕከላዊውን መንግሥት አደራጀ። ሶንግሃይ አካባቢ የነበሩ ነገዶችን በመውጋትም ግዛቱን አስፋፋ። የመሐመድ የፖለቲካ ብልጠት፥ አሊ በእስልምና ላይ የነበረውን ዝንባሌ እንዲለውጥ አደረገው። መሐመድ እስልምናን ለሥልጣኑ ማጠናከሪያ ቢጠቀምበትም፥ የእስልምናን እንቅስቃሴ አስነሥቷል የሚባለውን ገለጣ ግን የሚደግፍ በቂ መረጃ የለም። ስለዚህ፥ መሐመድ ቱሬ ሙስሊም




ቢሆንም፥ በእርእያነቱ አበረታታቸው እንጂ ሕዝቡ እንዲሰልም አላስገደደም። አንዳንድ ሞሮኳውያን በ1591 ዓ.ም. ዋና ከተማይቱን በወረሩ ጊዜ፥ የሶንግሃይ መንግሥት ሕልውና አከተመ።

ከነዚህ መንግሥታት በስተ ምሥራቅ ‘‘የማዕከላዊ ሱዳን መንግሥት’’ በመባል የሚታወቅ የምዕራብ አፍሪካ ክልል ይገኛል። በዚህ ክልል ከ800-1500 ዓ.ም. በነበረው ጊዜ ብዙ ትናንሽ መንግሥታትና ንጉሣዊ አገዛዞች ነበሩ። ከሁሉም ልቀው የሚታወቁት ካኒም ቦርኑ እና ሐውሳ የተባሉት ናቸው። የሐውሳ መንግሥታት የያዙት ዛሬ ሰሜን ናይጀሪያ የሚባለውን ክልል ነው። ካኒም ቦርኑ ደግሞ ከሐውሳ መንግሥታት በስተምሥራቅ ይገኝ ነበር። ስለ እነዚህ መንግሥታት ለመናገር በቂ ስፍራ የለንም። ቢሆንም እስልምና ወደ እነዚህ ክልሎች ስለገባበት ሁኔታ አንድ ወይም ሁለት እውነታዎችን ማንሣት አለብን። እስልምና ከ1085-1240 ዓ.ም. ካሊም ቦርኑ ውስጥ በመጠናከር ላይ እንደነበር ግልጥ ነው። ይሁን እንጂ ሃይማኖቱ የመሪዎችና የከተማ ሕዝቦች እምነት የነበረ ይመስላል። በገጠሩ የሚኖሩ ሕዝቦች ግን በአረማዊነታቸው ቀጥለዋል። እጅግ ብዙ ሰዎች ሙስሊም የሆኑት ከሁለት ወይም ሦስት ክፍለ ዘመናት በኋላ ነበር። እስልምና ወደ ሙስሊሙ ሰሜን አፍሪካ ለሚወስደው የነጋዴዎች የመጓጓዣ መንገድ ጠቃሚ ኬላዎች ወደሆኑት ካኒምና ሶንግሃይ ከማምራት ይልቅ፥ ወደ ሐውሳ ዘልቆ ገባ። እስከ አሥራ አምስተኛው ክፍለ ዘመን ከተሞችን መያዝ አልጀመረም ነበር። በአሥራ አምስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የሙስሊም ሚስዮናውያን ከምዕራብ ሱዳንና ከቦርኑ መምጣት፥ ካኖ ውስጥ የተካሄደው የከተማ ሃይማኖታዊ እንቅስቃሴ መሠረታዊ ለውጥ ከግብ እንዲደርስ አገዘ።




በ1500 ዓ.ም. አካባቢ ምዕራብ አፍሪካ ውስጥ የነበረውን ሁኔታ ለማጠቃለል ያህል፥ አብዛኛው ሕዝብ አሁንም የሚኖረው ከባሕሩ ዳርቻ እጅግ ራቅ ባለ ምድር ሲሆን፥ በባሕሩ ዳር በነበሩ ዝናባማ ደኖች ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች ቁጥር እጅግ ጥቂት ነበር ለማለት እንችላለን። እስልምና በ1500 ዓ.ም. በአብዛኛው የማዕከላዊ ምዕራብ አፍሪካ ክፍል ከገባ ሦስት ወይም አራት መቶ ዓመት አካባቢ ቢሆነውም፥ አስቀድመን እንደጠቀስነው በገጠሩ ሕዝቦች ዘንድ ገና ተቀባይነት በማግኘት ላይ ነበር።

አሁን ደግሞ ትኩረታችንን ወደ ደቡብ አፍሪካ መልሰን በክልሉ የነበሩትን ፖለቲካዊና ሃይማኖታዊ ሁኔታዎች እንመልከት። በመሠረቱ ከ1000 ዓ.ም. በፊት ከዛምቤዚ በስተደቡብ ስለነበሩት ሕዝቦች የሚታወቀው ነገር በጣም ጥቂት ነው። ይሁን እንጂ እንደሚያስታውሱት ምዕራፍ አንድ ውስጥ አፍሪካ በመጀመሪያው መቶ ክፍለ ዘመን ስለነበረችበት ሁኔታ በተመለከትን ጊዜ፥ ኮንጎ ወንዝ ሸለቆ ውስጥ ከነበሩት የባንቱ ቋንቋ ተናጋሪ አፍሪካውያን ብዙዎቹ ነገዶች ወደ ምሥራቅና ደቡብ ለሚጓዙበት ታላቅ ፍልሰት በመዘጋጀት ላይ ነበሩ ብለናል። ስለዚህ ከ100-1500 ዓ.ም. በነበረው ጊዜ የባንቱ ቋንቋ ተናጋሪ አፍሪካውያን ቀስ በቀስ ወደ ደቡብ አፍሪካ በመንቀሳቀስ ላይ ነበሩ ልንል እንችላለን። አንዳንድ የባንቱ ቋንቋ ተናጋሪ አፍሪካውያን የዛምቤዚን ወንዝ ያቋረጡት በ1000 ዓ.ም. ሳይሆን አይቀርም። ከዚያ በፊት በአካባቢው የሚኖሩት ብዙዎቹ የጥንት "የድንጋይ ዘመን" ቡሽሜን ይባሉ የነበሩት ናቸው።




የባንቱ ቋንቋ ተናጋሪ አፍሪካውያን ከተሻሻለው የእርሻ ዘዴያቸው ጋር በአካባቢው በደረሱ ጊዜ ግን፥ እነዚህን የጥንት ሰዎች ወደ ደቡብ ምዕራብ አቅጣጫ ገፏቸው።

ወደ ክልሉ የመጡት እነዚህ የመጀመሪያዎቹ የባንቱ ቋንቋ ተናጋሪ አፍሪካውያን፥ ከጊዜ በኋላ ኃይለኛና ጠንካራ ሕዝቦች የሆኑ የሾና ነገድ ቅድመ አያቶች ሳይሆኑ አይቀሩም። ቀደም ብለው የደረሱት የባንቱ ቋንቋ ተናጋሪ አፍሪካውያን በፍጥነት በማደግ ዛሬ ሮዴሺያ (ዚምባብዌ) ተብላ በምትጠራው ምድር የድንጋይ ሕንጻዎችን ይገነቡ ጀመር። እነዚህ አፍሪካውያን ከ1080-1450 ዓ.ም. በነበረው ጊዜ የመጀመሪያውን የድንጋይ ሕንጻ በዚምባብዌ የገነቡ ናቸው እየተባለ ይነገራል።

የዚምባብዌ ኢኮኖሚ የተመሠረተው በወርቅ ላይ ነበር። በአካባቢው ብዙ የወርቅ ማዕድን ስፍራዎች ነበሩ። ተቆፍሮ የሚወጣው ወርቅ ወደ ሞዛምቢክ ተልኮ በዕቃዎች ይለወጥ ነበር። ፖርቱጋሎች ሞዛምቢክ በደረሱበት በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን፥ ዚምባብዌ በወርቅ ምንጭነቷ የታወቀች አገር ነበረች።

ሮዴሺያና ሞዛምቢክ ውስጥ ምናልባት ሌሎች ነገዶች ኖረው ይሆናል። ቢሆንም የዚምብባዌን የሞኖማታፓ ሕዝቦች ያህል እድገት ማሳየታቸውን ይጠቁም ዘንድ የተውት ማስረጃ የለም።

ራቅ ባሉት የደቡብ ስፍራዎች ሌሎች የባንቱ ነገዶች ሰፍረው ይሆናል የሚል ግምት ቢኖርም፥ ማረጋገጡ ግን አስቸጋሪ ነው። አንዳንድ




የዓረብ ከተማና የንግድ መንገድ
በአሥራ አምስተኛው ክፍለ ዘመን

የታሪክ ሊቃውንት የባንቱ ነገዶች በ1500 ዓ.ም. ደቡብ አፍሪካ ውስጥ ደቡባዊውን ዳርቻ በመከተል ሰፍረው ነበር ብለው ያምናሉ። ብዙዎቹ የዘመናችን ነጭ ደቡብ አፍሪካውያን ከሚያምኑት በተጻራሪ፥ ደቡብ አፍሪካ በ1500 ዓ.ም. አያሌ ባንቱዎች ይኖሩባት እንደነበረ የታሪክ ገለጣዎች ያስገነዝቡናል። እንዲሁም የኬይ ወንዝ ምሥራቃዊ ክፍል የዙሉዎች ቅድመ አያቶች መኖሪያ እንደነበር እነዚሁ ታሪኮች ይነግሩናል። በአሥራ ስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ስለነበሩ የደቡብ አፍሪካ ሕዝቦች ከሆሳዎች፥ ከቴምቡሶች፥ ከፓንዶዎች እና ንጉኒዎች የምናውቀው ነገር ቢኖር ይኸው ነው። እነዚህ አካባቢዎች ያኔ እንደ ምዕራብ አፍሪካ መንግሥታት የሰለጠኑ እንዳልነበሩ ሊገመት ይገባል። ከዛምቤዚ ወንዝ በስተደቡብ የነበሩ ነገዶች በሙሉ እምነታቸው የአፍሪካ ባሕላዊ ሃይማኖት ነበር ለማለት እንችላለን።

በመጨረሻ ከ800-1500 ዓ.ም. የነበረውን ምሥራቅ አፍሪካ እንቃኝ። በመጀመሪያ የባሕሩን ዳርቻ ወይም ጠረፉን ስንመለከት፥ እስከ 1000 ዓ.ም. ድረስ በአካባቢው በዋናነት የሚኖሩ አፍሪካውያን ነበሩ። "እስከ 1150 ዓ.ም. ድረስ ከባራዋ ደቡብ የሚገኙ የዋናዋ ምድር ከተሞች ነዋሪዎች አረማውያን ስለነበሩ፥ እስከዚያን ጊዜ ድረስ በምድሪቱ የሰፈሩት ሙስሊሞች ቁጥር አነስተኛ መሆን አለበት።" ዓረቦች ከፋርስ ባሕረ-ሰላጤ አካባቢ መጥተው በባሕሩ ዳርቻዎች የሰፈሩት በአሥራ ሁለተኛውና አሥራ ሦስተኛው መቶ ክፍለ ዘመናት ነው። የንግድ ከተሞችን በመገንባት በባሕሩ ዳርቻ ከነበሩት አፍሪካውያን ጋር መቀላቀል ጀመሩ። በ1400 ዓ.ም. "ነዋሪዎቹ በዋናነት የሰፈሩባቸው ቦታዎች፥ በሦስት የተለያዩ ክፍሎች ወይም መደቦች እንደተከፋፈሉ ለመገመት ይቻላል። የገዢው መደብ አባላት የዓረብና አፍሪካዊ ዝርያ ድብልቅ የሆኑና መልካቸው የቀይ ዳማ የነበረ ሲሆኑ ጥሩ የእስልምና እውቀት ነበራቸው። የመሬት ከበርቴዎች እና የሰለጠኑ የኪነ ጥበብ ሰዎችም ይገኙባቸው ነበር። ብዙዎቹ የሃይማኖት አንቀሳቃሾችና ነጋዴዎች እነርሱ ሳይሆኑ አይቀሩም። ከነርሱ በታች ያሉት፥ (በብዙ ሁኔታ ባሪያዎች የሆኑት) እና ድብልቅ ያልሆኑት አፍሪካውያን፥ ዝቅተኛ ሥራዎች የሚሠሩ፥ እንዲሁም በእርሻ ሥራ የተሠማሩት ናቸው።

ከሁለቱ ሌላ፥ ጊዜያዊ ተንቀሳቃሽ ወይም በቅርብ ጊዜ የሰፈሩና ሙሉ ለሙሉ ከኅብረተሰቡ ያልተዋሀዱ ዓረቦች ይገኙ ነበር። በ1500 ዓ.ም. በጠረፉ የነበሩት ሙስሊሞች ተደላድለው ሠፈሩ። ወደ መካከለኛው ምሥራቅ አፍሪካ ዘልቀው ለመግባት ግን ጨርሶ አልሞከሩም። እስልምና ይህን ሥልጣኔ ለመንፈሳዊ መነቃቃት ይረዳው ዘንድ የሃይማኖቱን የትውልድ ስፍራ በሩቅ የሚያይበት የመመልከቻ ማማ እንደሆነ አድርጎ መቁጠር ይገባል። የእስልምና ሃይማኖት ከጠረፍ ሊያልፍ አልቻለም፤ ማራኪው የሕንጻ ጥበባቸውም በመሀል አገር ላይ ምንም ተጽዕኖ አልነበረውም። ፖርቱጋሎች ወደ አፍሪካ በደረሱ ጊዜ፥ ዓረቦች በምድሪቱ የሠፈሩ ቢሆንም፥ ባሕላቸውን ወይም እስልምናን በአካባቢው መሀል አገር ወደሚኖሩት አፍሪካውያን ለማድረስ ያደረጉት ሙከራ ግን አልነበረም።

ስለ ምሥራቅ አፍሪካ መካከለኛ ምድር ከ800-1500 ዓ.ም. ያለው ታሪክ የፍልሰትና የሠፈራ ነው። ሠፋሪዎቹ ከዓረብ ምድር ወይም ከሌላ አህጉር የመጡ አልነበሩም። ከ100 ዓ.ም. ጥቂት ዘግየት ብሎ፥ የመጀመሪያዎቹ አፍሪካውያን ወደ ምሥራቅ አፍሪካ መግባት ጀመሩ። እነዚህን ሕዝቦች በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ለመመደብ ይቻላል። ናይሎት የተባሉት ከሰሜን ወይም ከሰሜን ምዕራብ ወደ ምሥራቅ መጡ።




ምናልባትም ከደቡብ ሱዳንና ከኢትዮጵያ ምዕራባዊ ድንበር አካባቢ ይሆናል። ባንቱ የተባሉት የመጡት ደግሞ ከምዕራብ፥ ከደቡባዊ ምዕራብና ከምዕራብ አቅጣጫ ሳይሆን አይቀርም። ናይሎቶችም ሆኑ ባንቱኛ ተናጋሪ አፍሪካውያን ወደ ምሥራቅ አፍሪካ የመጡት፥ በአንድ ጊዜ አይደለም። የሁለቱም ሕዝቦች አያሌ ፍልሰቶች ወይም እንቅስቃሴዎች የተደረጉት የብረት ዘመን ይባል በነበረበት (ከ100 ዓ.ም.-1800 ዓ.ም.) ጊዜ እንደሆነ መገመት አለብን።

በአሥራ ስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ምሥራቅ አፍሪካ ውስጥ ስለ ሰፈሩት ነገዶች በዝርዝር ለመናገር በቂ ስፍራ የለንም። በሚገባ ከሚታወቁት የምሥራቅ አፍሪካ የጥንት ሥልጣኔዎች አንዱ፥ ችዌዚ ይባሉ የነበሩት ከብት አርቢ ሕዝቦች ታሪክ ነው።

እነዚህ ሕዝቦች ወደ ዩጋንዳና ሰሜን ታንዛኒያ የመጡት ከሱዳን ወይም ከኢትዮጵያ ነው። በአፈ ታሪክና በከርሰ ምድር ጥናት መረጃ መሠረት፥ የችዌዚዎች ባሕል ከ1350-1500 ዓ.ም. በነበረው ጊዜ የበለጸገ መሆን አለበት። ይህ ነገድ ከ1500 ዓ.ም. በኋላ ጠፍቶ በሌሎች ነገዶች የተተካ ይመስላል። በ1500 ዓ.ም. የመጀመሪያው የሉኦ ጎሳ ምዕራብ ኬንያ ውስጥ የሠፈረና የባንቱ ጎሳ ቅድመ አያት የሆኑት ኩኩዩዎች እንዲሁም

አካምባዎች ወደ ሰሜን ለመንዝ የታኢታን ኮረብታማ አካባቢዎች ለቀቁ ለማለት ይቻላል። የባንቱ ቋንቋ ተናጋሪ አፍሪካውያንም በታንዛኒያ ተስፋፍተው ነበር። በዚህ ጊዜ የነበረውን የምሥራቅ አፍሪካ ሃይማኖታዊ ሁኔታ በተመለከተ፥ አብዛኞቹ የጠረፍ ከተሞች ነዋሪዎች የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ይሁኑ እንጂ፥ የመሀሉ አገር ነዋሪዎች ግን የባሕላዊ ሃይማኖት ተከታዮች ነበሩ ለማለት ይቻላል።

ቅኝታችንን ለማጠቃለል ያህል፥ በ1500 ዓ.ም. አፍሪካ ሰፊ ሥልጣኔ የነበራት፥ በደቡቡ ክፍል የነበሩትን ሥልጣኔ ያልነካቸው የጫካ ሰዎች ጨምሮ የሰሜኖቹን ሥልጡን የጠረፍ በርበሮች የያዘች ሰፊ አህጉር ነበረች። በኢትዮጵያና በግብፅ በሁለት ትናንሽ አካባቢዎች ጥቂት ሰዎች የኮፕቲክ ቤተ ክርስቲያን አባላት የነበሩ ከመሆኑ በስተቀር፥ አብዛኛዎቹ አፍሪካውያን ኢየሱስ ክርስቶስ ኃጢአተኞችን ለማዳን ወደ ዓለም መምጣቱን አያውቁም ነበር። ያኔ የአሕጉሪቱ አብዛኛው ሕዝብ የሚከተለው የአፍሪካን ባሕላዊ ሃይማኖት ሲሆን፥ ሁለተኛውን ስፍራ የሚይዘው እስልምና ነበር። ክርስትና እጅግ ርቆ ሦስተኛውን ስፍራ ነበር የያዘው። ጊዜው ቤተ ክርስቲያን በሁለተኛው፥ በሦስተኛውና በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን እንዳደረገችው፥ አፍሪካን በወንጌል ለመድረስ ሌላ ሙከራ የምታደርግበት ትክክለኛ ወቅት መስሎ ነበር።

# የአፍሪካ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ የጊዜ ሰሌዳ 100-1950 ዓ.ም.

(በተለያዩ የአፍሪካ ክፍሎች ከተፈጸሙት ታሪካዊ ድርጊቶች መካከል የተመረጥት ያላቸውን ግንኙነት ለማሳየት)

| ዘመን | ሰሜን አፍሪካ | በምዕራብ አፍሪካ | ማዕከላዊ አፍሪካ | ደቡብ አፍሪካ | ምሥራቅ አፍሪካ |
|---|---|---|---|---|---|
| 100 | ቤተ ክርስቲያን ግብፅ ውስጥ በማደግ ላይ ስትሆን፥ በካርታጎ ደግሞ ገና በመቆርቆር ላይ ነበረች።<br>ክርስቲያኖችን ለማሰልጠን መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ቤት ግብፅ ውስጥ ተከፈተ። | የምዕራብ ሱዳን ቋንቋ ተናጋሪ ነገዶች ምዕራብ አፍሪካ ውስጥ ሰፍረው ነበር። | የባንቱ ቋንቋ ተናጋሪ አፍሪካውያንን ያቀፈ ትልቅ ቡድን ኮንጎ ወንዝ አጠገብ ነበር። | ሆቴንቶቶችና የድንጋይ ዘመን ነገዶች ይህን ስፍራ መኖሪያ አደረጉት። የአፍሪካ ነገዶች ገና እስፍራው አልደረሱም ነበር። | ከሰሜን ምሥራቅ የተነሡ የኒሎቲክ ሕዝቦች ወደ ምሥራቅ አፍሪካ መፍለስ ጀመሩ። |
| 200 | ተርቱሊያን ካርታጎ ውስጥ የነበረበት ጊዜ | | | | ከኮንጎ ወንዝ ዳርቻ የተነሡ የባንቱ ቋንቋ ተናጋሪ አፍሪካውያን ወደ ምሥራቅ አፍሪካ መግባት ጀመሩ። |
| 250 | ሲፕሪያን የካርታጎ ጳጳስ ሆኖ ተመረጠ።<br>ሮማውያን በቤተ ክርስቲያን ላይ ስደት አስነሡ። | የምዕራብ አፍሪካ ሕዝቦች የባሕል ሃይማኖቶችን ይለማመዱ ጀመር። | የኮንጎ ሕዝቦች ባሕላዊ የነገድ ሃይማኖት ይከተሉ ነበር። | | |
| 300 | አርዮሳዊነት ቤተ ክርስቲያንን ከፋፈላት። | | | ሆቴንቶቶችና ሌሎች የጥንት ነገዶች የራሳቸውን ባሕላዊ ሃይማኖቶች መከተል ቀጠሉ። | ፍሬምናጦስ ወንጌልን ወደ ኢትዮጵያ ወሰደ። |
| 350 | ዶናቲሳውያን የካርታጎን ቤተ ክርስቲያን ከፋፈሏት።<br>የአውግስጢኖስ ወደ ክርስትና መለወጥ | | | | የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በፍሬምናጦስ የመጀመሪያ ጳጳስነት ተመሠረተች። |
| 400 | ቫንድሎች ሰሜን አፍሪካን ወረሩ።<br>የአፍሪካ አብያተ ክርስቲያን | | | | |
| 450 | በክርስቶስ ባሕርይ ላይ ለመነጋገር ጳጳሳትን ወደ ኬልቄዶን ላኩ። | | | | |

| ዘመን | ሰሜን አፍሪካ | ምዕራብ አፍሪካ | ማዕከላዊ አፍሪካ | ደቡብ አፍሪካ | ምሥራቅ አፍሪካ |
|---|---|---|---|---|---|
| 500 | የኮፕቲክ ቤተ ክርስቲያን፥ ኢየሱስ መለኮታዊ ባሕርይ ብቻ ነው ያለው በሚል እምነት ግብፅ ውስጥ ተመሠረተች። | በምዕራብና በሰሜን አፍሪካ መካከል የነበረው ንግድ ጨመረ። | | | የሲሪያ ሚስዮናውያን (ሞኖፎሳይታውያን) የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ኮፕቲክ እንድትሆን አሳመኗት። ጁሊያን ወንጌልን ወደ ኑብያ አመጣ። |
| 550 | የግብፅ የቢዛንታይን ቤተ ክርስቲያን ማሽቆልቆል | | | | ሎንጂነስ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ለመንገር ወደ ኑብያ መጣ። ኢትዮጵያውያን መጽሐፍ ቅዱስን ወደ ግዕዝ ተረጎሙ። |
| 600 | አሚር ግብፅን በመውረር እስልምናን ወደ አፍሪካ አመጣ። | | | | |
| 650 | ኡክባ የአፍሪካን ክልላዊ ግዛቶች ወረረ። ሐሰን ካርታጎን ያዘ። | | | | ኑብያኖች በጠረፍ ሰላምን ለመጠበቅ ከግብፅ ዓረቦች ጋር ስምምነት ተፈራረሙ። |
| 700 | በአፍሪካና በካርታጎ ያሉ አብያተ ክርስቲያን በውስጥ ድካምና በእስልምና ግፊት ምክንያት በፍጥነት ማሽቆልቆል ጀመሩ። | | | | ኑብያኖች እስልምና ወደ ኑብያ እንዳይገባ ተከላከሉ። |
| 750 | በግብፅ የነበሩ የኮፕቲክ ክርስቲያኖች ቁጥር በሙስሊሞች ከሚደረግባቸው ግፊት የተነሣ ማሽቆልቆል ጀመረ። | | | | |

| ዘመን | ሰሜን አፍሪካ | ምዕራብ አፍሪካ | ማዕከላዊ አፍሪካ | ደቡብ አፍሪካ | ምሥራቅ አፍሪካ |
|---|---|---|---|---|---|
| 800 | የሰሜን አፍሪካ ቤተ ክርስቲያን በፍጥነት ማሽቆልቆል ጀመረች። | የጋና መንግሥት በሥልጣን ይስፋፋ ጀመር። ከሰሜን አፍሪካ ጋር የሚደረገው የንግድ ግንኙነት አደገ። | | | ኮፕቲክ ቤተ ክርስቲያን በኢትዮጵያ እድገቷን ቀጠለች። |
| 850 | የበርበር ነገድ ሰዎች ወደ እስልምና መመለስ ጀመሩ። | | | | |
| 900 | በዚህ ጊዜ አብዛኛው ሕዝብ ሙስሊም ነበር። | በሰሜንና በምዕራብ አፍሪካ መካከል የወርቅና የጨው ንግድ ይበልጥ ተስፋፋ። | | | የደቡብ አረማውያን ነገዶች በኢትዮጵያ ላይ የሚያደርጉት ጦርነት የኢትዮጵያን ኃይል በከፍተኛ ሁኔታ አዳከመው። |
| 1000 | የካርታጎና የአፍሪካ ጳጳሳት ቁጥር በ650 ዓ.ም. 40 ከነበረበት በ1050 ዓ.ም. ወደ 6 ወረደ። | የጋና ነገሥታት እስልምናን ተቋቋሙ። ሙስሊም በርበሮች ጋናን ማጥቃት ጀመሩ። | | | የዓረብ ጀልባዎች የምሥራቅ አፍሪካን የባሕር ዳርቻ መጎብኘት ጀመሩ። |
| 1100 | ሙስሊም በርበሮች የሰሜን አፍሪካ መንግሥታትን ለመለወጥ መሞከር ጀመሩ። | የጋና መንግሥት በበርበሮች እጅ ወደቀ። | | | የኢትዮጵያ ነገሥታት አረማውያንን ድል አድርገው ግዛታቸውን አጠናከሩ። |
| 1150 | | | | | ዓረቦች በምሥራቅ አፍሪካ የባሕር ዳርቻዎች የንግድ መተላለፊያ አበጁ። |
| 1200 | በርበሮች ሰሜን አፍሪካ ውስጥ የነበራቸውን የበላይነት ያጡ ጀመር። | ሰንዲያታ ኬይታ የማሊን መንግሥት ገነባ። | | | |

| ዘመን | ሰሜን አፍሪካ | ምዕራብ አፍሪካ | ማዕከላዊ አፍሪካ | ደቡብ አፍሪካ | ምሥራቅ አፍሪካ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1250 | የግብፅ ሙስሊሞች የኑብያ ዋና ከተማ የሆነችውን ዶንጎላን ያዙ ። | | | | በኢትዮጵያ አዲስ ሥርወ-መንግሥት ተመሠረተ፥ አዲሱ ንጉሥ ክርስቲያኖች ብርቱዎች እንዲሆኑ አበረታታቸው። |
| 1300 | | ማንሳ ሙሳ ማሊን ወደ ከፍተኛ የኃይል ደረጃ አደረሳት፤ ወደ መካ የተቀደሰ ጉዞ አደረገ። | | | |
| 1350 | ሃፍሲዶች የማዕከላዊ ሰሜን አፍሪካ መሪ ሆኑ። | የሶንግሃይ መንግሥት ይጠነክር ጀመር። | | | |
| 1400 | ዋታሲዶች የሰሜን አፍሪካን ምዕራባዊ ክፍል አስተዳደሩ። | የፖርቱጋል መርከቦች ሴኔጋል ወንዝ ጫፍ ደረሱ። | | | ዘርዓ ያዕቆብ የኢትዮጵያ ንጉሥ ሆነ። የኮፕቲክን ቤተ ክርስቲያን ከሙስሊሞች ሊጠብቅ ፈለገ (1434 ዓ.ም.)። |
| 1450 | | ሱኒ አሊ የሶንግሃይ ንጉሥ ሆነ (1464 ዓ.ም.)። | | | በባሕሩ ዳርቻ የነበሩ ሙስሊሞች ኢትዮጵያን መውጋታቸውን ቀጠሉ። |
| 1500 | ምዕራባዊ ሰሜን አፍሪካ ውስጥ የምትገኘው ቤተ ክርስቲያን ሙሉ በሙሉ ጠፋች። | | የካቶሊክ ሚስዮናውያን ከንጎ መንግሥት ግዛት ደረሱ (1491 ዓ.ም.)። | ዲያዝ ኬፕ አፍ ጉድ ሆፕ ደረሰ (1487 ዓ.ም.)። | ቫስኮ ደጋማ ሞምባሳና ማሊንዲ ደረሰ (1498 ዓ.ም.) |
| 1550 | ሳአዲያኖች የሰሜን ምዕራብን ክልል አስተዳደሩ። የነቢዩ መሐመድ ዝርያዎች ነበሩ። | ሶንግሃይ በሞሮኳውያን ወራሪ ቡድን ድል ሆንና የመጨረሻው ታላቅ መንግሥት አበቃ (1591 ዓ.ም.)። | አልፎንሶ የመጀመሪያው የኮንጎ ክርስቲያን ንጉሥ ሆነ። | ዳ ሲልቬኢራ ሞኖማታፓን ለመለወጥ በመሞከር ላይ ሳለ ተገደለ (1561 ዓ.ም.)። | 400 የፖርቱጋል ወታደሮች የኢትዮጵያን ንጉሥ ከሙስሊም ወራሪዎች አዳኑት (1541 ዓ.ም.)። |

| ዘመን | ሰሜን አፍሪካ | ምዕራብ አፍሪካ | ማዕከላዊ አፍሪካ | ደቡብ አፍሪካ | ምሥራቅ አፍሪካ |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | የመጀመሪያው የካቶሊክ ገዳም ሞምባሳ ውስጥ ታነጸ (1567 ዓ.ም.)። |
| 1600 | | አውሮፓውያን በባሕር ዳርቻ መሥመር ላይ የንግድ ኬላዎችን ገነቡ። | | | ኢየሱሳውያን ኢትዮጵያውያን ኮፕቲክ ክርስቲያኖችን ወደ ካቶሊክ እምነት ለመለወጥ ይጥሩ ጀመር። (1607 ዓ.ም.)። |
| 1650 | | በባሕር ዳርቻው መሥመር ላይ የባሪያ ንግድ ተጀመረ። | ኮንጎ መንግሥት ውስጥ የካቶሊክ እምነት ማሽቆልቆል ጀመረ። | | ካቶሊኮች ከኢትዮጵያ ተባረሩ (1625 ዓ.ም.)። |
| 1700 | የተለያዩ ቅዱሳት ማራበውተሶችን (የተቀደሱ ስፍራዎችን) በመገንባት አብዛኛውን የምሮኮ ክፍል ተቆጣጠሩ። | | | የሞሬቪያኑ ሽምት በገጠሩ ክፍል ሰበከ። ሽምት ክርዕሰ ምድሩ በደቾች ተባረረ። | በሙስሊሞች ጠላትነት የተነሣ ካቶሊካዊ እምነት በሞምባሳ አከተመ። |
| 1750 | | ቶምፕሰን በኬፕ የባሕር ዳርቻ ለእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን መሥራት ጀመረ (1751 ዓ.ም.)። ፊሊፕ ኩዋኮ በኬፕ የባሕር ዳርቻ መስበክ ጀመረ (1766 ዓ.ም.)። | የካቶሊክ እምነት ኮንጎ ውስጥ አከተመ። | የሞሬቪያን ሁለተኛ ቡድን ኬፕ ደረሰ (1792 ዓ.ም.)። | ምሥራቅ አፍሪካ የባሕር ዳርቻ ላይ ይካሄድ የነበረው የባሪያ ንግድ ጨመረ። |
| 1800 | ነጭ አበው ካቶሊካውያን የሚስዮን ሥራ አልጄሪያ ውስጥ ጀመሩ። | የመጀመሪያው የቤተ ክርስቲያን ሚስዮናውያን ማኅበር ሴራሊዮን ውስጥ ተቋቋመ (1804 ዓ.ም.)። | | የለንደን ሚስዮናዊ ማኅበር ደቡብ አፍሪካ ውስጥ ሥራውን ጀመረ (1799 ዓ.ም.)። ዴቪድ ሊቪንግስተን ኬፕታውን ደረሰ (1840 ዓ.ም.)። | ክራፍ የመጀመሪያውን የቤተ ክርስቲያን ሚስዮናውያን ማኅበር ጣቢያ ሞምባሳ ውስጥ አቋቋመ (1844 ዓ.ም.)። |

| ዘመን | ሰሜን አፍሪካ | ምዕራብ አፍሪካ | ማዕከላዊ አፍሪካ | ደቡብ አፍሪካ | ምሥራቅ አፍሪካ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1850<br>1900<br>1950 | የሰሜን አፍሪካ ሚስዮን በአልጄሪያ ሥራ ጀመረ (1881 ዓ.ም.)።<br>የወንጌል ሚስዮናውያን ኅብረት ሞሮኮ ውስጥ ሥራ ጀመረ (1895 ዓ.ም.)።<br>ጣሊያን የሊቢያን መንግሥት ከተቆጣጠረች በኋላ የሮም ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን የሚስዮናዊነት ሥራ በሊቢያ ጀመረች። | ዊሊያም ዲ ግራፍት የመጀመሪያውን የአፍሪካ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ጋና ባሕር ዳርቻ ላይ መሠረተ።<br>ቄስ ሳሙኤል ክሮውዘር ወደ ናይጀር ጉዞ አድርጎ፥ የእንግሊዝ ጳጳስ ሆኖ ተሾመ (1864 ዓ. ም.)።<br>አውሮፓውያን አፍሪካን ለመያዝ ተሽቀዳደሙ።<br>የሴራሊዮን የእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን የራሷን ሚስዮናውያን ላከች (1895 ዓ.ም.)።<br>ነቢዩ ሃሪስ በአይቮሪኮስትና በጎልድ ኮስት ሰበከ (1914 ዓ.ም.)።<br>ዋና ዋና የእምነት ክፍሎች (ዲኖሚኔሽንስ) ከውጭ ሚስዮናውያን ተላቀው ራሳቸውን ቻሉ። | የሮም ካቶሊኮች ኮንጎ አካባቢ እንደገና ሚስዮናዊ ሥራ ጀመሩ።<br>ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው የፕሮቴስታንት ሚስዮናውያን ኮንጎ ገቡ።<br>የፕሮቴስታንት ሚስዮናውያን ኮንጎ የሚገኘውን የሊዎፖልድ አሰቃቂ ወንጀል የዓለም ሕዝብ እንዲያውቀው አደረጉ።<br>ስምኦን ኪምባንጉ የራሱን መንፈሳዊ ቤተ ክርስቲያን ኮንጎ ውስጥ መሠረተ።<br>አዲሱ የትምህርት አመራር የፕሮቴስታንት ትምህርት ቤቶች እንዲስፋፉ እገዛ አደረገ። | የሬኒሽ ሚስዮን ደቡብ ምዕራባዊ አፍሪካ ውስጥ ሥራ ጀመረ።<br>በደቡብ አፍሪካ የመጀመሪያይቱ ነጻ መንፈሳዊት ቤተ ክርስቲያን ተመሠረተች (1892 ዓ.ም.)።<br>ጆን ቺሌምብዌ በኒያሳላንድ በተደረገ ዓመፅ የራሱን ባፕቲስቶች መራቸው (1915 ዓ.ም.)።<br>የደቡብ አፍሪካ መንግሥት ቤተ ክርስቲያን የምታስተዳድራቸውንና የምትረዳቸውን ትምህርት ቤቶች በቅርብ መቆጣጠር ጀመረ። | የሮም ካቶሊኮች ነጻ ለወጡ ባሪያዎች ታንጋኒካ ውስጥ የሚስዮን ጣቢያ ከፍተውላቸው ወደ ምሥራቅ አፍሪካ ተመለሱ።<br>የዩጋንዳ ሰማዕታት ስለ እምነታቸው ካምፓላ አጠገብ በምትገኝ ስፍራ ተገደሉ (1886 ዓ.ም.)።<br>የአፍሪካ ኢንላንድ ሚስዮን ወንጌልን ወደ ኬንያ መካከለኛ ስፍራ አደረሰ (1895 ዓ.ም.)።<br>ሩዋንዳ ውስጥ ሪቫይቫል (መንፈሳዊ እንቅስቃሴ) ተጀመረ። (1928 ዓ.ም.)።<br>ዋና ዋና የእምነት ክፍሎች (Denomina-tions/ ዲኖሚኔሽንስ) ቁጥር ከውጭ ሚስዮን ነጻ ሲሆኑ አብያተ ክርስቲያኑ እየተስፋፉ ሄዱ። |

# - 10 -

# የፖርቱጋሎች ሚስዮናዊ ተግባር 1450-1750 ዓ.ም.

በአሥራ አምስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ፥ ከአውሮፓ ባሻገር የቀረውን ዓለም ለማወቅ ከፍተኛ ፍላጎት የነበረውና ሄንሪ የሚባል የፖርቱጋል ልዑል ነበር። ስሙ ልዑል ሄንሪ ቢሆንም፥ ስለ አትላንቲክ ውቅያኖስ ይበልጥ ለመረዳት ከነበረው ከፍተኛ ፍላጎት የተነሣ፥ "መርከበኛው" በመባል ይታወቃል። የአውሮፓ ሕዝቦች በአሥራ አራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ገደማ የሰሜንና የደቡብ አሜሪካ አህጉራት መኖራቸውን አያውቁም ነበር። ከሰሐራ በረሃ በስተደቡብ ስላለው የአፍሪካ ክፍል እንኳን የሚያውቁት ብዙ ነገር አልነበረም። አትላንቲክ ውቅያኖስ ለአውሮፓውያኑ እጅግ ትልቅና የሚያስፈራ ስለነበር፥ በመርከብ የሚጓዙት ከምድር ብዙም ሳይርቁ ነው። ሜዲትራኒያን ባሕር ላይ ብቻ ነበር በነጻነት የሚንቀሳቀሱት። ስላልታወቀው ነገር ከነበራቸው ፍርሃት የተነሣ፥ ከአሥራ አምስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በፊት በመርከቦቻቸው ወደ አፍሪካ ወይም ወደ ህንድ አይጓዙም ነበር።

በ1420 ዓ.ም. አካባቢ ልዑል ሄንሪ ስለ ውቅያኖሱ ይበልጥ ለማወቅ፥ በተለይም የምዕራብ አፍሪካን ወርቅና የህንድን ቅመማ ቅመም ለማግኘት የሚያስችሉትን የባሕር ላይ መተላለፊያዎች ለማግኘት ይጥር ጀመር። በዚህ ጊዜ የሰሜን አፍሪካ ሙስሊሞች የምዕራብ አፍሪካን የወርቅ ንግድ፥ የመካከለኛው ምሥራቅ ሙስሊሞች ደግሞ የቻይናን ሐርና የህንድን የቅመም ንግድ ይቆጣጠሩ እንደነበር መታወስ አለበት። እነዚህ ሁሉ ነገሮች የሚያልፉት በዓረብ ወይም በበርበር ምድሮች ስለሆነ፥ ሙስሊሞች ቀረጥ ያስከፍሉ ነበር። በትራንስፖርትና በዚህ የቀረጥ ወጭ ምክንያት ወርቅና ቅመማ ቅመም በአውሮፓ በውድ ይሸጡ ጀመር። ስለዚህ ልዑል ሄንሪ በሰሜን አፍሪካና በመካከለኛው ምሥራቅ ሙስሊሞች ዙሪያ የሚያሳልፉ የባሕር ላይ መንገዶች ለመፈለግ በጣም ተነሣሣ።

ልዑል ሄንሪ ከ1421-1445 ዓ.ም. ባለው ጊዜ ብቻ ከአሥር የሚበልጡ ተጓዦችን ላከ። ጉዞው ከእነሣሡ እጅግ ዝግ ያለ ስለነበር፥ ከተጓዦቹ አንዱ ካፕቴን ምዕራብ አፍሪካ ዳር ካለው ሴኔጋል ወንዝ የደረሰው በ1445 ዓ.ም. ነው። ልዑል ሄንሪ የሞተው የትኛውም መርከብ ኬፕ ኦፍ ጉድ ሆፕ [Cape of Good Hope] ወደሚባለው ስፍራ ከመድረሱ በፊት በ1460 ዓ.ም. ነው። ይህ ከመሆኑ ቀደም ብሎ ግን የፖርቱጋል የንግድ መርከቦች በባሕሩ ዳርቻ ካሉት አፍሪካውያን ጋር ንግድ ለመለዋወጥ፥ በምዕራብ አፍሪካ የባሕር ዳርቻ የማያቋርጥ ጉዞ ያደርጉ ነበር።




የፖርቱጋል መርከበኞች በአፍሪካ የባሕር ዳርቻዎች ወደፊት መግፋታቸውን ቢቀጥሉም፥ በጊዜው የታየው እድገት እጅግ አነስተኛ ነው። ካፕቴን ዲኦጎ ጋም የተባለው መርከበኛ እንኳን እስከ 1484 ዓ.ም. ድረስ ታላቁ የኮንጎ ወንዝ መግቢያ አልደረሰም። ከደረሰ በኋላ ግን የኮንጎ ንጉሣዊ መንግሥት አባላት የሆኑ ጥቂት ወዳጆች አፈራ። የመንግሥቱ አባላት የሆኑት ኮንጎዎች፥ በክልሉ ያሉ ሰፊ ጎሳዎች ነበሩ። በ1487 ዓ.ም. በርቶሎሚ ዲያዝ የተባለው መርከበኛ ኬፕ ኦፍ ጉድ ሆፕ ከተባለው ስፍራ ደረሰና፥ ወደ ፖርቱጋል ከመመለሱም በፊት እስከ ደቡባዊ የአፍሪካ ጫፍ ተጓዘ።

ቫስኮ ደጋማ ታሪካዊዎቹን አዳዲስ ቦታዎች አስሶ የማግኘት ጉዞውን በሐምሌ ወር 1497 ዓ.ም. ጀምሮ፥ በጥር ወር 1498 ዓ.ም. አፍሪካ ምሥራቃዊ ዳርቻ ጫፍ ወዳለ የዛምቤዚ ወንዝ መግቢያ ደረሰ። ከዚያም በባሕሩ ዳር የሚገኙትን የተለያዩ የዓረብ ከተሞች እየጎበኘ ወደ ሰሜን ተጓዘ። በ1498 ዓ.ም. ማሊንዲ ሲደርስ፥ ህንድን እስኪያገኝ ድረስ ህንድ ውቅያኖስ ላይ የመራውን አንድ ዓረባዊ መርከበኛ አገኘ። ስለዚህ ፖርቱጋሎች በሙስሊሞች ቁጥጥር ሥር የነበሩ አገሮችን ሳይነካ ህንድ የሚያደርሳቸውን መንገድ ለማግኘት ያደርጉት የነበረ ሙከራ በ1498 ዓ.ም. ግቡን መታላቸው።

እነዚህ በፖርቱጋሎች የተደረጉ አዳዲስ ስፍራዎችን ፈልጎ የማግኘት ጉዞዎች ሁሉ፥ በአፍሪካ የክርስትና ታሪክ ላይ ያመጡት ለውጥ

ምንድነው? ልዑል ሄንሪ የመጀመሪያዎቹን መርከቦች ለአሰሣ በሚልክበት ጊዜ የነበረውን ዓላማ ወደ ኋላ መለስ ብለን ብንመለከት፥ የዚህ ጥያቄ መልስ ቀላል ይሆንልናል። ልዑሉ ስለ ውቅያኖሱ ይበልጥ ለማወቅና አዳዲስ የንግድ መሥመሮችን ለመፈለግ ከነበረው አሳብ በተጨማሪ አፍሪካ ውስጥ ክርስቲያን ነገሥታት እንዳሉ ለማወቅ ይፈልግ ነበር። "ፕሬስተር ጆን" የሚባል ጠንካራ ክርስቲያን ንጉሥ፥ አፍሪካ ውስጥ አለ የሚል ወሬ በአውሮፓ ይወራ ስለነበር፥ ልዑል ሄንሪ ያን ንጉሥ ለማግኘት ፈለገ። ከዚሁ ጋር የሮም ካቶሊክ ሚስዮናውያን ፖርቱጋሎች የንግድ ማዕከላት ላቋቋሙባቸውና በአፍሪካ ጠረፎች ለሚገኙት ሕዝቦች፥ ሁሉ የክርስትናን መልእክት እንዲያደርሱ ይፈልግ ነበር።

በዚህ ሁኔታ ነበር የካቶሊክ ሚስዮናውያን ከቀድሞዎቹ የፖርቱጋል የንግድ መርከቦች ጋር የተጓዙት። በ1462 ዓ.ም. የሮሙ ጳጳስ ለምዕራብ አፍሪካ ሚስዮናውያን ሁሉ ኃላፊ የሚሆን ሰው ሾመ። እስከ ክፍለ ዘመኑ መጨረሻ ድረስ በዚህ አካባቢ ብዙ ሚስዮናውያን የሠሩ ቢሆንም፥ ወደ ክርስትና እውነተኛ ለውጥ ያደረጉት ሰዎች ግን ጥቂት ነበሩ። የአፍሪካውያን ፍላጎት ያረፈው ከፖርቱጋሎች ሃይማኖት ይልቅ፥ ባመጡት ጠመንጃና ሥልጣን ላይ ይመስል ነበር። ስለሆነም ፖርቱጋሎች ጊዜና ገንዘባቸውን ከቤተ ክርስቲያን ሥራ ይልቅ ለንግድ ማስፋፋት ስላዋሉት፥ የሚስዮናዊነት ተግባር ብዙ ትኩረት ሳይሰጠው ቀረ።

ፖርቱጋሎች ራቅ ባሉት የደቡብ አካባቢዎች ይበልጥ ውጤታማ ሆነዋል። ታሪኩ የጀመረው ዲአጎ ጋም የተባለው መልእክተኛቸው የኮንጎን ወንዝ መዳረሻ በ1484 ዓ.ም. በጎበኘ ጊዜ ነው። ሰውዬው ስፍራውን በጎበኘ ጊዜ በጣም ተግባቢ ከሆኑ ጥቂት አፍሪካውያን ተገናኘ። ከነዚህ ጥቂቱን ወደ ፖርቱጋል በመውሰድ አውሮፓን ሊያሳያቸው ወሰነ። በዚሁ መሠረት ወደ ፖርቱጋል የሚወስዳቸውን አፍሪካውያን፥ ባሪያዎች እንደማያደርጋቸው ለማረጋገጥ ወይም ዋስትና ለመስጠት ሲል፥ ከፖርቱጋል ባሕርተኞች ጥቂቶቹን እዚያው ትቷቸው ሄደ። እነዚህ አፍሪካውያን ባኮንጎ የሚባለው ንጉሣዊ መንግሥት አባላት ነበሩ።

የኮንጎ ንጉሣዊ አገዛዝ በአሥራ አራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጨረሻ፥ ወይም በአሥራ አምስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የመጀመሪያ ዓመታት ከደቡብ ምሥራቅ በመጣው ወራሪ ቡድን የተመሠረተ ዓይነተኛ 'ሱዳናዊ' መንግሥት ነበር። ይህ ንጉሣዊ አገዛዝ በ1450 ዓ.ም. ዋና ከተማውን ምባንዛኮንጎ ያደረገና የተደራጀ ሆኖ ነበር። ምባንዛኮንጎ በአሁኑ ጊዜ ሰሜን አንጎላ ውስጥ የምትገኝና ሳን ሳልቫዶር ተብላ የምትጠራ ከተማ ናት። የዚህ መንግሥት ሕዝብ ብዛት ሁለት ሚሊዮን ተኩል ያህል ይገመት ነበር። ይህ የሚያመለክተው የአካባቢው ነዋሪ አንድ ትልቅ ሕዝብ እንጂ አነስተኛ ነገድ እንዳልነበረ ነው።

በ1485 ዓ.ም. ፖርቱጋሎች የወሰዷቸውን አፍሪካውያን ወደ ምባንዛኮንጎ መለሷቸው። እነዚህ ሰዎች ፖርቱጋልኛና የክርስትናን መሠረታዊ እውነቶች በአንድ ዓመት ውስጥ ተምረው ነበር። የፖርቱጋል ንጉሥ በነዚህ ሰዎች አማካይነት ማኒኮንጎ ይባል ለነበረው የባኮንጎ ንጉሥ ስጦታ ላከለት። ማኒኮንጎ፥ ሰዎቹ ባመጡለት ዜናና ከአውሮፓ በተላከለት ስጦታ እጅግ ተደንቆ፥ የሚረዱት ሚስዮናውያንን ይልኩለት ዘንድ ፖርቱጋሎችን ጠየቀ። በዚሁ መሠረት የመጀመሪያዎቹ የካቶሊክ ሚስዮናውያን በ1491 ዓ.ም. እስፍራው ደረሱ።

ለሚስዮናውያኑ የተደረገው አቀባበል እጅግ መልካም ከመሆኑም በላይ፥ በመጀመሪያው ዓመት ብዙ ሰዎች ወደ ክርስትና ተለወጡ። ከተለወጡት ሰዎች መካከል ንጉሡ፥ ሚስቱና ትልቁ ልጃቸው ይገኙበት ነበር። ንጉሡና ንግሥቲቱ እውነተኛ ውሳኔ ያደረጉ አልመሰሉም። በኋላ አልፎንሶ በመባል የተጠራው ልጃቸው ግን እራሱን የሰጠ እውነተኛ ካቶሊክ ሆነ። የንጉሡ ሁለተኛ ልጅ ክርስትናን አልቀበልም ከማለቱም በላይ፥ የተለወጡ ሰዎች ተፃራሪ ሆነ። በዚሁ መሠረት ሚስዮናውያኑ ከአንድ በላይ ጋብቻን በመቃወም ይሰብኩ ስለነበር አስቸጋሪ ጊዜ ገጠማቸው። ክርስቲያኖች ከአንድ በላይ ጋብቻን መቃወማቸው ከፍተኛ ተቃውሞ አስነሣባቸው። የቀድሞው እምነት አክራሪዎች በክርስትና ትምህርት እጅግ ተከፉ። ንጉሡ የክርስትናን እምነት ካደ፤ አልፎንሶም ተሰደደ። በዚህም የተነሣ ሚስዮናዊው ድርጅት ያለ አንዳች እርዳታ ቀረ።

ከጥቂት ጊዜ በኋላ በአልፎንሶና በወንድሙ መካከል ጦርነት ተካሂዶና፥ አልፎንሶ ድል አድርጎ የባኮንጎ ንጉሥ በመሆኑ፥ የክርስቲያን መንግሥት መሠረተ። ወዲያው ብዙ ሚስዮናውያን ወደ ኮንጎ መጡ። ሆኖም ሥራቸው በሕዝቡ ውስጥ ሥር ሊሰድ የቻለ አይመስልም። ቢሆንም አልፎንሶ፥ ከሕዝቡ መካከል ብዙ ሰዎችን ለክህነትና ለመንግሥት ሥልጣን ሥልጠና ወደ ፖርቱጋል ላከ። ኮንጎ ውስጥ ብዙ ሰዎች በፖርቱጋል የጥምቀት ስም ሲጠሩ፥ የመንግሥቱም አመራር እንደ አብዛኛው የአውሮፓ መንግሥታት ሆነ። አልፎንሶ በሞተበት በ1543 ዓ.ም. የካቶሊክ አማኞች ነን የሚሉ ሰዎች ቁጥር በምድሪቱ እጅግ ብዙ ነበር።

ከ1543 ዓ.ም. በኋላ የኮንጎ መንግሥት አልተሳካለትም። ፖርቱጋሎች ከአፍሪካ ወስደው ብራዚል ውስጥ የሚያሠራቸውን ባሪያዎች በማግኘቱ ተግባር ላይ ይበልጥ አተኮሩና ከኮንጎ በስተደቡብ ከምትገኘው አንጎላ ባሪያዎችን መግዛት ጀመሩ። በመሆኑም የአንጎላ ሰዎች ባሪያዎች ለማግኘት ኮንጎን ጨምሮ በዙሪያቸው ከሚገኙ ነገዶች ጋር ጦርነት ማድረግ ነበረባቸው።

ከአልፎንሶ ቀጥሎ የተነሡ ነገሥታት ክርስትናን ብዙም ስላልወደዱት፥ ሕዝቡ ከካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ይርቅ ጀመር። በዚህ ሳቢያ በኮንጎ ንጉሣዊ አገዛዝ ውስጥ የነበረው ክርስትና በ1700 ዓ.ም. አከተመ። በኮንጎ የነበረው ሚስዮን፥ ከጥንታዊቱ ቤተ ክርስቲያን ምሥረታ ወዲህ በመታወቅ ረገድ የመጀመሪያው ሲሆን፥ ከሰሐራ በረሃ በስተደቡብ ደግሞ በየትኛውም ተከታታይ ታሪክ የሚቀድመው የሌለ ቢሆንም የኋላ ኋላ ጠፋ። በእስልምና ተሸንፎ ሳይሆን፥ እንዲሁ የጠፋ ነው የሚመስለው።

ፖርቱጋሎች ከኤክዋቶር በስተደቡብ ክርስትናን ለማስተዋወቅ የሞከሩት ኮንጎ ውስጥ ብቻ አልነበረም። በአፍሪካ በስተምሥራቅ በንግድ ምክንያት ከባሕር ዳርቻው ጋር ግንኙነት የነበራቸው በርካታ ነገዶች ይኖሩ ነበር። በ1560 ዓ.ም. ዳ ሲልቬኢራ የተባለ የፖርቱጋል ሚስዮናዊ በምድሪቱ ለመኖርና ሞኖማታፓ ከተባሉት ሕዝቦች ጋር ለመሥራት ሰፋላ ወደምትባለው አካባቢ መጣ። በመጀመሪያ ወደ ሞዛምቢክ ከተማ፥ ከዚያም ወደ ውስጥ ዘልቆ ሴና ወደተባለችው የንግድ ስፍራ አመራ። እዚያ ሆኖ ወደ ሞኖማታፓ ንጉሣዊ ግዛት ለመግባት ፈቃድ ይጠብቅ ጀመር። በመጨረሻ ፈቃድ አገኘና ታኅሣሥ 25 ቀን 1560 ዓ.ም. ወደ ዋናይቱ ከተማ ገባ። ንጉሡና፥ ንጉሣውያን ቤተሰቡ በሲልቬኢራ የአጭር ጊዜ የክርስትና ትምህርት አምነው ተጠመቁ። ከተማው ውስጥ የነበሩ ሙስሊም ነጋዴዎች ይህን ሲመለከቱ ፖርቱጋሎች የወርቅ ንግድን ይቀሙናል ብለው ፈሩ። ስለዚህ ወደ ንጉሡ በመሄድ ዳ ሲልቬኢራ ንጉሡን በማጥመቅ እርግማን ያመጣበት ብልኀ ጠንቋይ እንደሆነ ነገሩት። እርግማኑ የሚቆምበት ብቸኛው መንገድም ዳ ሲልቬኢራን መግደል ነው አሉት። በዚሁ መሠረት ዳ ሲልቬኢራ በመጋቢት ወር 1561 ዓ.ም. ሞኖማታፓ ከተማ ውስጥ ተገደለ።

ከዳ ሲልቬኢራ ሞት በኋላ ሌሎች የፖርቱጋል ሚስዮናውያን ቴቴ ወደተባለው ስፍራና የሞኖማታፓ አንዳንድ ክፍሎች ወንጌልን ለመስበክ ሄደው ነበር። ሚስዮናውያኑ በ17ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ብዙ ሰዎችን አጥምቀዋል። የተለወጡት ሰዎች የሚያደርጉትን የሚያውቁ መሆናቸው ግን የሚያጠራጥር ነበር። ጠንካራና ፈጣን እድገት የሚታይባት ቤተ ክርስቲያን በአካባቢው አልነበረችም። በዚህ ምክንያት ብዙ ሰዎች ወደ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን መምጣታቸውን የሚገልጥ ሁኔታ ያለ አይመስልም። የሞኖማታፓ ንጉሥ በ1652 ዓ.ም. ተጠመቀ። ድርጊቱ ፖርቱጋሎችን እጅግ ደስ ቢያሰኛቸውም፥ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን በስፍራው የምታደረገው ሚስዮናዊ ጥረት ግን በመዳከም ላይ ነበር። ቤተ ክርስቲያኖቹም እንዲሁ እየተዳከሙ ሄዱ። በአሥራ ስምንተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ወደ ውስጥ ዘልቆ ለመሥራት የሞከረ ሚስዮናዊ አልነበረም።




በመሆኑም በክፍለ ዘመኑ መጨረሻ በመሀል አገር የነበረችው የፖርቱጋሎች ቤተ ክርስቲያን ሞተች።

ፖርቱጋሎች በምሥራቅ አፍሪካ የባሕር ዳርቻ ከፍተኛ ስፍራዎች የሚገኙ አፍሪካውያንን ወደ ክርስትና በመለወጡ ተግባር ውጤታማ አልሆኑም። ወደ ኬንያ ዘልቆ ለመግባት እንኳ ብዙ ጥረት የተደረገ አይመስልም። ያደረጉት ነገር ቢኖር፥ ኪልዋ እና ሞምባሳ የተባሉትን ከተሞች የራሳቸው ለማድረግ ምሽጎችን መገንባት ነው። እነዚህን ስፍራዎች ወደ ህንድ ለሚሄዱ መርከቦቻቸው ማረፊያ ያደርጓቸው ነበር። ብዙ የፖርቱጋል ሚስዮናዊያን ቡድኖች ከ1500-1700 ዓ.ም. በነበረው ጊዜ ወደ ምሥራቅ አፍሪካ ቢመጡም፥ ወደ ደቡብ የተሠማሩት ሚስዮናውያን አፍርተናል የሚሉትን ያህል ብዙ የተለወጡ ሰዎች አላገኙም። የአውግስጦስያውያን ካህናት ቡድን በ1567 ዓ.ም. ሞምባሳ ላይ አንድ ገዳም ሠሩ። በ1598 ዓ.ም. ሦስት ሚስዮናውያን ካህናት ላሙ ወደተባለ ስፍራ ተጓዙ። ሥራቸው የቆየው ግን ለጥቂት ዓመታት ነበር። ቀጥሎ የሰማነው ነገር የአውግስጦስያውያን መነኮሳት ሞምባሳ ደሴት ላይ በ1598

ዓ.ም. ዛሬ ጥንታዊው የባሕል አዳራሽ በሚገኝበት ስፍራ አንድ ቤተ ክርስቲያን መገንባታቸውንና ወዲያውኑ ከአካባቢው ሕዝብ መካከል 600 ሰዎች ወደ ክርስትና የተለወጡ መሆናቸውን ነው። በ1607 ዓ.ም. አዲስ የካቶሊክ ሚስዮናዊ ማኅበረሰብ ሞምባሳ ደረሰ። የማኅበሩ አባላት የምሕረት ወንድማማች በመባል ይጠሩ የነበረ ሲሆን፥ ዋና ሥራቸውም ከእስልምና ወደ ክርስትና ለተለወጡ ሰዎች እንክብካቤ ማድረግ ነበር። በአሥራ ሰባተኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጨረሻ ፖርቱጋሎች የምሥራቅ አፍሪካ ይዞታቸውን ያጡ ጀመር። የካቶሊክ ሚስዮናውያን ተግባር ማሽቆልቆል የጀመረውም በዚሁ ጊዜ ነው። በአሥራ ዘጠነኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ ከአንዳንድ የውጭ አገር ነጋዴዎች በስተቀር በባሕሩ ዳርቻ የቀሩ ካቶሊኮች አልነበሩም።

የፖርቱጋል ሚስዮናውያን ከ1450-1750 ዓ.ም. ድረስ በአፍሪካ ያከናውኑትን ተግባር የሚመለከተው ጥናታችን የመጨረሻ ክፍል ወደ ኢትዮጵያ ይወስደናል። ኢትዮጵያን ለመጎብኘት የመጀመሪያው የሆነው ፖርቱጋላዊ ኢትዮጵያ የደረሰው በ1487 ዓ.ም. ሲሆን፥ የኢትዮጵያ ንጉሥ እዚያው እንዲቀርና እንዲኖር አስገደደው። በ1520 ዓ.ም. አንድ የፖርቱጋሎች ቡድን ወደ ኢትዮጵያ በመጣ ጊዜ ክርስቲያናዊ የነበረውን የኢትዮጵያ ዙፋናዊ መንግሥት አጠና። ፖርቱጋሎች ፕሬስተር ጆን በሚባል ንጉሥ የሚመራ አንድ የክርስቲያን መንግሥት በመፈለግ ላይ እንደነበሩ ሊታወስ ይገባል። ስለዚህ ኢትዮጵያንና ክርስቲያን ንጉሥዋን ሲያገኙ "የፕሬስተር ጆንን መንግሥት" እንዳገኙ አመኑ። መንግሥቱ የጠበቁትን ያህል ጠንካራ ያለመሆኑና፥ ኢትዮጵያውያን የኦርቶዶክስ ክርስትና ሃይማኖታቸውን የሚከታተሉበት ሁኔታ ከካቶሊካዊ ሥርዓት የተለየ የመሆኑ ጉዳይ በመጠኑ አሳዝኗቸው ነበር።

አገሪቱን በሙስሊሞች ድል ከመሆን ያዳናት የፖርቱጋል መልእክተኞች ቡድን በ1541 ዓ.ም. ኢትዮጵያ መድረሱን ምዕራፍ ሰባት ውስጥ ተመልክተናል። ከዚያ ወዲህ የፖርቱጋል ሚስዮናውያን ወደ ኢትዮጵያ ይላኩ ጀመር። የኢትዮጵያ ነገሥታት፥ ቤተ ክርስቲያናቸው የሮም ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን አካል እንድትሆን ስለማይፈልጉ፥ መጀመሪያ ፖርቱጋሎችን ጠርጥረዋቸው ነበር። ስለሆነም የመጀመሪያዎቹ ሚስዮናውያን እንዲሠሩ የተፈቀደላቸው፥ አክሱም አቅራቢያ በሚገኘው ፍሬሞና በተባለ ስፍራ ነበር። በዚሁ መሠረት ፓኤዝ የተባለ ሚስዮናዊ ሥራውን እንዲያግዝ በ1603 ዓ.ም. ፍሬሞና ደረሰ። ቋንቋዎችን በቀላሉ የመማር ተሰጥኦ ስለነበረው በአጭር ጊዜ ውስጥ የግዕዝን ቋንቋ ማንበብ፥ መጻፍና መናገር ጥሩ አድርጎ ተማረ። ፓኤዝ ተግባሩን በጸጥታና በዝግታ በማከናወን ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ለመገንባት ተግቶ ሠራ። ሥራው ውጤታማ የሆነለት፥ ንጉሥ ሱስንዮስ ካቶሊካዊ መሆኑን በግልጥ

በተናገረበት በ1622 ዓ.ም. ነበር። ከዚያ በኋላ ፓኤዝ ብዙም ሳይቆይ ሞተ።

ፓኤዝን ተክቶ ሥራውን ለመምራት የተላከው አዲስ ሚስዮናዊ ሜንዴዝ ይባል ነበር። ሜንዴዝ በጣም ብልህ አልነበረም። የኮፕቲክን ቤተ ክርስቲያን በፍጥነት የሮም ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን አካል አድርጎ ለመለወጥ ሞከረ። ሕዝቡ ዳግም እንዲጠመቁ ከማስገደዱም በላይ፥ የኮፕቲክን ቤተ ክርስቲያን እንደገና እቀድሳለሁ አለ። ይህ ሁኔታ ሕዝቡን ለዓመፅ ጋበዘ እንጂ አልጠቀመም። ይህን አዲስ ዓይነት ክርስትና ሕዝቡ ስላልፈለገው የእርስ በርስ ጦርነት ተነሣ። በዚህ ሳቢያ ንጉሡ ከዙፋኑ እንዲወርድና፥ በስፍራው ልጁ እንዲተካ የሚያስገድድ ሁኔታ ተፈጠረ። ልጁም ኢየሱሳዊ በመባል የሚታወቁትን የካቶሊክ ሚስዮናውያን በሙሉ በማባረር፥ የኮፕቲክ ቤተ ክርስቲያን እንደማትቀየር በግልጥ አወጀ። ይህ አዋጅ ሕዝቡን ደስ አሰኛቸውና የእርስ በርሱ ጦርነት አበቃ።

የኢትዮጵያ ኮፕቲክ ቤተ ክርስቲያን ፖርቱጋሎች በሚጎበኟት ጊዜ ምን ትመስል ነበር? ከፖርቱጋል ሚስዮናውያን አንዱ የጻፈው አጭር መግለጫ አለን። ይህ መግለጫ ስለ ኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ብዙ ይነግረናል። በዚሁ ጽሑፉ "አብዛኛው የቤተ ክርስቲያናቸው የአምልኮ ሥርዓትና ክንዋኔ ከሮም ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ጋር የሚመሳሰል ነው" ብሏል። ሎቦ የተባለ ይኼው ሚስዮናዊ የጻፈው የሚከተለው ነው። "የጌታችንን ሥቃይ መታሰቢያ በዓል የሚያከብሩት ታላቅና ጥልቅ በሆነ የሃይማኖተኛነት ስሜት ነው። መስቀሉን ያከብራሉ፥ ለተባረከችው ድንግል፥ ለመላእክትና ለቅዱሳን ከፍተኛ አክብሮት ያሳያሉ። በዓላትን ያከብራሉ፥ ሰንበትንም በልዩ ትኩረት ይጠብቁታል። የድንግል ማርያምን እርገት መታሰቢያ በዓል በየወሩ ያከብራሉ። ለአምላክ እናት እውነተኛውን ክብር እየሰጠ እንደነሱ የሚያከብራት ክርስቲያን የለም ብለው ያስባሉ። በየሳምንቱም ለመላእክትና ለሐዋርያት ክብር ይደግሳሉ። ለማስቀደስ ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚሄዱትም በታላቅ የአምልኮ መንፈስና፥ የእግዚአብሔርን ቃል ለማድመጥ በጉጉት ነው። ራሳቸውን በንስሐ ባያዘጋጁም ብዙ ጊዜ ቅዱስ ቁርባን ይወስዳሉ።" በአምልኮ ጊዜ ኃይል የሚሻ አካላዊ እንቅስቃሴ፥ ሁካታና ጫጫታ ብዙም ተቀባይነት እንዳልነበረው ነው ሎቦ የተረዳው። "እንደ አቢሲኒያ በአብያተ ክርስቲያን፥ በገዳማትና በካሕናት የተሞላ አገር አልነበረም። ከአብያተ ክርስቲያኑና ከገዳማቱ መቀራረብ የተነሣ፥ በአንደኛው ውስጥ ሲቀደስ ወይም ሲዘመር በሌላው፥ ምናልባትም በብዙዎቹ ዘንድ ሳይሰማ ሥርዓቱን ለማከናወን አይቻልም። የዳዊትን መዝሙሮችና የቅዱሳት መጻሕፍትን ሌሎች ክፍሎች ያዜማሉ። የቅዱሳት መጻሕፍቱ ትክክለኛ ትርጉም

በራሳቸው ቋንቋ አላቸው። በአምልኮ ጊዜ የሚጠቀሙባቸው የሙዚቃ መሣሪያዎች፥ በአንገታቸው በሚያጠልቁት ጠፍር የሚያንጠለጥሏቸውና በእጃቸው የሚደልቋቸው ከበሮዎች ናቸው። ቅላፄያቸውን የሚጀምሩት መሬቱን በእግሮቻቸው በመርገጥና የዝማሬ መሣሪያዎቻቸውን በዝግታ ወይም ለስለስ አድርገው በመጫወት ሲሆን፥ ቀስ በቀስ ዝማሬው ሲደምቅ፥ ከበሮውን በኃይል በመደለቅ መዝለል፥ ማሽብሸብ፥ ማጨብጨብ ይጀምራሉ። ከዚያም ከአጀማመሩ የነበረው ዝግታና ሥርዓት ዝብርቅርቅ ያለ እስኪመስል ድረስ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው በመዘመር ይወዛወዛሉ።"

ይህ ፖርቱጋሎች ከ1450-1750 ዓ.ም. በነበረው ጊዜ በአፍሪካ ስላደረጉት ሚስዮናዊ እንቅስቃሴ የምናደርገውን ጥናት ወደ ማጠቃለሉ ያመጣናል። ይህን ምዕራፍ ከመዝጋታችን በፊት ግን ሁለት ጥያቄዎችን ለመመለስ መሞከር ይኖርብናል።

1) ያን ጊዜ የፕሮቴስታንት ሚስዮናውያን የት ነበሩ?

2) ለምን ነበር ፖርቱጋሎች እስከ መጨረሻው የምትዘልቅ ቤተ ክርስቲያን መመሥረት ያቃታቸው?

ብዙ ሰዎች አፍሪካ ውስጥ ከ1450-1650 ዓ.ም. ክርስትናን ለመጀመር ጥረት ስላደረጉት የካቶሊክ ሚስዮናውያን ብቻ የምናነበው ለምን እንደሆነ ለማወቅ ይፈልጋሉ። ፕሮቴስታንቶች ሚስዮናውያን ያልላኩት ለምን እንደነበር ለማወቅ በመፈለግ፥ ግድ ስላልነበራቸው ነውን? ብለውም ይጠይቃሉ። ይህን ጥያቄ ለመመለስ ማርቲን ሉተር የፕሮቴስታንት ተሐድሶን (Reformation) የጀመረበትን ትክክለኛ ጊዜ ከቤተ ክርስቲያን ታሪክ መመልከት ያሻል። ማርቲን ሉተር የተሀድሶ መነሻ የሆኑ ጥያቄዎቹን ጀርመን ዊትንበርግ ከተማ ቤተ ክርስቲያን በር ላይ የለጠፈው በ1517 ዓ.ም. ነበር። ይህ ዓመተ ምሕረት ፖርቱጋሎች ሚስዮናውያኖቻቸውን ወደ አፍሪካ መላክ ከጀመሩ ሰባ ዓመታት በኋላ መሆኑ ይታወሳል። ስለዚህ ከ1440-1520 ዓ.ም. በነበረው ጊዜ ሚስዮናውያንን ወደ አፍሪካ ይልኩ የነበሩ የሮም ካቶሊክ ሚስዮናውያን ብቻ የመሆናቸው የመጀመሪያ ምክንያት የፕሮቴስታንት ቤተ ክርስቲያን ገና በአውሮፓ ያልተመሠረተች መሆኑ ነበር።

ከ1520 ዓ.ም. በኋላ ብዙ የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያን በአውሮፓና በእንግሊዝ ቢመሠረቱም፥ ብዙ ጊዜ በካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ይሰደዱና ችግር ይደርስባቸው ነበር። እነዚህ ፕሮቴስታንቶች ከ1520-1700 ዓ.ም. በነበረው ጊዜ እራሳቸውን ከሮም ካቶሊኮች ነጻ ለማድረግ በመከላከሉ ተግባር ተወስነው ነበር። ከዚሁ ጋር በዙሪያቸው

ያሉትንና በቤዛነት በፈሰሰው በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ስለሚገኘው ደኅንነት ጨርሰው ሰምተው የማያውቁትን ሰዎች የመድረስና በወንጌል የመማረክ ታላቅ ተግባር ነበረባቸው። ስለዚህ እስከ አሥራ ስምንተኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጨረሻ አካባቢ በፕሮቴስታንት ሚስዮናውያን ተግባር ከፍ ያለ እንቅስቃሴ እንዳልታየ እንገነዘባለን። ያን ጊዜ የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያን ሰሜን አውሮፓና ሰሜን አሜሪካ ውስጥ በሚገባ በመመሥረት ወደ አፍሪካና ሌሎች የዓለም ክፍሎች ለመድረስ ተዘጋጅተው ነበር።

ሁለተኛው ጥያቄ "ፖርቱጋሎች ዘላቂ የሆነች ቤተ ክርስቲያን ለመመሥረት ያልቻሉት ለምን ነበር?" የሚለውና መልስ ለመስጠት ጥቂት አስቸጋሪ የሆነው ነው። የችግሩ ዋነኛ ምክንያት ፖርቱጋሎች ለንግድና ለሀብት የነበራቸው ታላቅ ፍላጎት ይመስላል። ሚስዮናዊውን ተግባር ቢያበረታቱም፥ ብዙ ባሪያዎች ፈልገው ሚስዮናውያኑ እንቅፋት በሚሆኑባቸው ጊዜ ግን፥ ንግዱን ለማብዛት ሲሉ ሚስዮናዊውን ጥረት ይተውት ነበር።

ሁለተኛው ችግር፥ የሚያገለግሉበትን አፍሪካዊ ባሕል በሚገባ አለመረዳታቸው ነበር። ለምሳሌ የሮም ካቶሊኮች፥ ወደ እነርሱ እምነት የተለወጡ ሰዎች ከአንድ ሚስት በላይ ማግባት እንደሌለባቸው ሲያዙ፥ ባሎቻቸው ለሚተዋቸው ሚስቶች ተገቢው እንክብካቤ እንዲደረግላቸው የሚያስችል ሁኔታ አያመቻቹም ነበር።

ቤተ ክርስቲያን የወደቀችበት ሌላ ምክንያት፥ ሚስዮናውያኑ ሕዝቡን ወዲያውኑ በብዛት ማጥመቃቸው ነው። ማለት ብዙ ሰዎችን ያጠምቃሉ፤ ሰዎቹ ግን ብዙውን ጊዜ የተከናወነው ነገርና የጥምቀት ትርጉሙ ምን እንደሆነ የተረዱ አልነበሩም። ስለዚህ ሚስዮናውያኑ ከስፍራው በሄዱ ጊዜ እነዚህ "የተለወጡ" ሰዎች አባላት ናቸው የተባሉበትን እምነት በሚገባ ስላልተረዱት፥ በክርስትና እምነት ለረጅም ጊዜ አልጸኑም። ፖርቱጋሎች አፍሪካውያኑን ስለ ክርስቶስ ትምህርቶች በሚገባ ለማስተማር ጨርሶ ሙከራ እንዳላደረጉ ነው ይህ ሁኔታ የሚያመለክተው።

## ጥያቄዎች

1. መርከበኛው ልዑል ሄንሪ ማን ነበር? የአፍሪካን ቤተ ክርስቲያን ታሪክ በመረዳት ረገድ ጠቃሚ የሆነውስ ለምንድነው?

2. በኮንጎ ንጉሣዊ አገዛዝ ውስጥ ስለተደረጉት ሚስዮናዊ ጥረቶች ባጭሩ ይግለጡ።

3. ክርስትና ወደ ሞኖማታፓ ለመውሰድ ጥረት ያደረገው ሚስዮናዊ ማን ነው? ምንስ ደረሰበት?

4. ከ1500-1700 ዓ.ም. በነበረው ጊዜ በሮም ካቶሊካዊ ሚስዮን አማካይነት ኬንያ ውስጥ የተከናወነውን ተግባር በአጭሩ ይግለጡ።

5. የሮም ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን የኢትዮጵያን ኮፕቲክ ቤተ ክርስቲያን መቆጣጠሩ የተሳናት ለምንድነው?

# - 11 -

# መጠነኛ የክርስትና እድገት የታየበት 18ኛው መቶ ክፍለ ዘመን

ከ1450-1700 ባለው ጊዜ አፍሪካ ውስጥ አብዛኛውን የሚስዮናዊነት ተግባር ያከናወኑት ፖርቱጋላውያን ካቶሊኮች መሆናቸውን ባለፈው ምዕራፍ ተመልክተናል። እስከ አሥራ ሰባተኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ድረስ ፕሮቴስታንት ሚስዮናውያን ስላደረጉት ጥረት የምናነበው ነገር የለም። ያኔ የተደረጉት ጥረቶችም ቢሆኑ አነስተኛና ውጤት አልባዎች ነበሩ። የተሻለ እንቅስቃሴ ያሳዩት በአሥራ ስምንተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ነው። ያም ቢሆን ከአሥራ ዘጠነኛው መቶ ክፍለ ዘመን እንቅስቃሴያቸው ጋር ሲነጻጸር በጣም ጥቂት ይመስላል።

በአሥራ ሰባተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የእንግሊዝና የደች ነጋዴዎች ምዕራብ አፍሪካ ውስጥ ፖርቱጋሎችን ይወዳደሯቸው ጀመር። በዚሁ መሠረት እንግሊዞችና ደቾች ወዲያውኑ ጎልድ ኮስት (ጋና) እተባለው ስፍራ ላይ የንግድ ኬላዎችን ሠሩ። ኬላዎቹ ውስጥ የክርስቲያን ነጋዴዎችን መንፈሳዊ ሁኔታ የሚጠብቁ ቄሶች ወይም መጋቢያን ነበሩ። መጋቢያኑ አንዳንድ ጊዜ በየኬላው ዙሪያ ካሉት አፍሪካውያን ጋር ግንኙነት ያደርጉ ነበር። ጥረቱ ግን ዘላቂ ውጤት አላስገኘም።

በ1652 ዓ.ም. ደቾች ደቡብ አፍሪካ፥ ኬፕታውን ውስጥ ማኅበር ወይም መንደር መሠረቱ። ዋና ዓላማቸው በአካባቢው የእርሻ መሬት ማልማትና ንግድ ማዳበር ሆኖ፥ ከዚሁ ጋር የመጀመሪያ ፍላጎታቸው ሆቴንቶቶች የተባሉ ጎሳዎችን ወደ ክርስቶስ ማምጣት ነበር። የደች ተሀድሶ (Reformed/ሪፎርምድ) ቤተ ክርስቲያን መጋቢያን እዚያ የነበሩትን ለመለወጥ ያደረጉት የመጀመሪያ ጥረት አልተሳካም።

ስለዚህ በአሥራ ስምንተኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ በአፍሪካ የምንመለከተው የፕሮቴስታንት ሚስዮናውያን ጥረት በደቡብ አፍሪካና በአሁኒቱ ጋና (ጎልድ ኮስት) የነበረው ደካማ ሥራ ብቻ ነበር። ልንረሳው የማይገባ ነገር ግን፥ የአውሮፓ ፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያን ዕድሜ ከ200 ዓመታት ያነሰ እንደሆነና፥ እስከ አሥራ ስምንተኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጨረሻ ድረስ አብያተ ክርስቲያኑ ብዙ ሚስዮናውያንን ለማስማራት ፍላጎቱም ሆነ የገንዘብ አቅሙ ያልነበራቸው መሆኑ ነው።

በአሥራ ስምንተኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ አንድ የክርስቲያኖች ቡድን ጀርመን ውስጥ በሚገኝ አንድ ትልቅ የእርሻ ስፍራ ሰፈረ። የዚህ ቡድን አባላት የሆኑት ክርስቲያኖች ሞሬቪያን ወንድማማቾች

በመባል የሚታወቁ ሲሆን፥ የፕሮቴስታንት ሚስዮናውያን ጥረት ወደፊት እንዲገፉ እጅግ የጣሩ ናቸው። ዋናው ፍላጎታቸው፥ ሕዝቦች ሁሉ የኢየሱስ ክርስቶስን መልካም የምሥራች እንዲሰሙ ማድረግ ነበር። የመጀመሪያዎቹን ሚስዮናውያኖቻቸውን በ1732 ዓ.ም. ወደ ምዕራብ ኢንዲስ፥ በ1737 ዓ.ም. ደግሞ ወደ አፍሪካ ላኩ።

ወደ አፍሪካ የተላከው የመጀመሪያ ሚስዮናዊ፥ ጆርጅ ሽምት የሚባል ሲሆን፥ ዋና ዓላማው ደቡብ አፍሪካ ኬፕ አካባቢ ለሚገኙትና ሆቴንቶቶች ለተባሉ ጎሳዎች ወንጌልን ማድረስ ነበር። ሽምት ይህን ያደረገው፥ በአካባቢው የሠፈሩት ደቾች ለነዚህ ሕዝቦች ስለ ወንጌል የመንገር ፍላጎት እንደሌላቸው በመረዳቱ ነው። ከኬፕታውን በስተ ምሥራቅ አንድ መቶ ስልሳ ኪሎ ሜትር ርቆ በሚገኝ ስፍራ ሥራውን ጀመረ። የሆቴንቶቶችን ቋንቋ ለመናገር ከፍተኛ ፍላጎት ቢኖረውም፥ ቋንቋቸውን ለመማርም ሆነ ለመናገር አዳጋች የሚያደርጉት ሦስት ዓይነት የንግግር ድምፆች እንዳሉ ተገነዘበ። በመሆኑም ያመጣውን መልእክት ለማስተላለፍ የነርሱን ቋንቋ ለመማር ከመጣር ይልቅ፥ የደች ቋንቋን ለነርሱ ማስተማሩን መርጦ ይህንኑ አደረገ።

በ1742 ሽምት አያሌ ሆቴንቶቶች ክርስቶስን እንደ አዳኛቸው መቀበላቸውን አይቶ ሊያጠምቃቸው ቢፈልግም፥ የቤተ ክርስቲያን መጋቢ ስላልነበረ፥ ሹመቱን ይሰጠው ዘንድ፥ ጀርመን የሚገኘውን የሚስዮን ቦርድ በደብዳቤ ጠየቀ። የጠየቀውን ሹመት ካገኘ በኋላ ሁለት ሆቴንቶቶችን አጠመቀ። አንዳንድ የደች አጥቢያ አብያተ ክርስቲያን መጋቢያን፥ የጀርመኑ ሚስዮናዊ (ሽምት) የቤተ ክርስቲያናቸውን ሰዎች ያጠመቀባቸው መሆኑን ተረድተው ችግር ባይፈጥሩበት ኖሮ፥ የሽምት ጅማሬ በሆቴንቶት ብርቱ ቤተ ክርስቲያን የመመሥረቻ መነሻ ይሆን ነበር። በሽምት ድርጊት ያልተደሰቱት እነዚህ መጋቢያን፥ ሽምት ያካሄደው የጥምቀት ሥርዓት ትክክል ስላልሆነ፥ ድርጊቱን በአካባቢው እንዲቀጥል ሊፈቀድለት አይገባም በማለት ቅሬታቸውን ኬፕታውን ውስጥ ገለጡ። እንዲህ በማድረግ ሥራውን እጅግ ስላከበዱበት በ1744 ዓ.ም. ወደ አውሮፓ መሄድ ግድ ሆነበት። ከዚያ ወዲህ እንደገና ወደ ደቡብ አፍሪካ ተመልሶ ሥራውን ለመቀጠል ጥረት ቢያደርግም፥ ደቾች የማይፈቅዱለት ሆነ። ስለዚህ በሆቴንቶቶች መካከል ያከናውነው የነበረ ሚስዮናዊ ተግባር ቆመ። ከዚያ ወዲህ ከእነዚህ ሕዝቦች ጋር የሚሠራ ሌላ ሚስዮናዊ የመጣው ከአምሳ ዓመት በኋላ ነበር።

ቀደም ብለው ከተቋቋሙት ማኅበሮች አንዱ በ1701 ዓ.ም. በእንግሊዝ የተቋቋመውና የወንጌል ሥርጭት ማኅበር በመባል የሚታወቀው ነው። የማኅበሩ አባላት አብዛኛዎቹን ሚስዮናውያኖቻቸውን የላኩት ወደ

ሰሜን አሜሪካ ነበር። በ1750 ዓ.ም. ግን በሰሜን አሜሪካ ይሠሩ ከነበሩ ሚስዮናውያኖቻቸው መካከል አንዱ በአፍሪካውያን መካከል ይሠራ ዘንድ ወደ ምዕራብ አፍሪካ እንዲልኩት ጠየቀ። በዚህ ጥያቄ መሠረት የተላከው ቶማስ ቶምፕሰን የተባለው ሚስዮናዊ በ1751 ዓ.ም. ዛሬ ጋና ተብላ ከምትጠራው ምድር ደረሰ።

ቶምፕሰን ሥራው አስቸጋሪ ሆኖ አገኘው። በንግድ መለዋወጫ ስፍራዎች የኖሩት አፍሪካውያን የአውሮፓ ነጋዴዎችን ሕይወት ለብዙ ዓመታት ሲመለከቱ ቆይተዋል። እነዚህ ሰዎች ክርስቲያን ነን እያሉ ብዙ ክፉ ሥራዎችን ሲፈጽሙ እየተመለከቱም ታዝበዋቸዋል። በመሆኑም ቶምፕሰን እስፍራው በደረሰና ለአፍሪካውያን አገልግሎት መስጠት በጀመረ ጊዜ፥ ብዙ ሰዎች መልእክቱን ለመስማት ፈቃደኞች አልነበሩም። ቶምፕሰን ከአፍሪካውያን ጋር ከመሥራት ሌላ አውሮፓውያን ነጋዴዎችን ጭምር በወንጌል የመድረስ ፍላጎት ነበረው። ነገር ግን በአፍሪካውያኑም ሆነ በአውሮፓውያኑ ዘንድ ተሰሚነትን አጣ። ቢሆንም ለአራት ዓመታት በትጋት ከሠራ በኋላ ታመመና ወደ እንግሊዝ ተመለሰ።

ኬፕ ኮስት በተባለው ስፍራ የተደረገው ወንጌል የማሠራጨት ጥረት ታሪክ በቶማስ ቶምፕሰን ወደ አገሩ መመለስ አያበቃም። ቶምፕሰን እስፍራው በነበረባቸው የመጀመሪያ ሦስት ዓመታት ለክርስቶስ የማረካቸው ጥቂት ሰዎች ነበሩ። ከነዚህ መካከል እጅግ ንቁ የሆኑ ሦስት ወጣቶችን በማግኘቱ፥ ወደ እንግሊዝ አገር ሄደው እንዲማሩ በ1754 ዓ.ም. ሁኔታዎችን አመቻቸላቸው። ትምህርታቸውን በትጋት በመከታተል ላይ ሳሉ፥ ሁለቱ ሞቱና ፊሊፕ ኩዋኬ የተባለው ብቻ ትምህርቱን አጠናቀቀ። ፊሊፕ ኩዋኬ ሥልጠናውን ፈጽሞ የእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን አባል ሆነ። ከቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ ወዲህ ከአውሮፓውያን ሌላ አባል በመሆን የመጀመሪያው ነበር። በ1765 ዓ.ም. የወንጌል ሥርጭት ማኅበር አባላት ኩዋኬን የሚስዮናቸው ትምህርት ቤት ኃላፊና፥ ጋና ለሚገኙት ጥቁሮች የመሠረተ እምነት ትምህርት መምህር አድርገው ሾሙት።

ኩዋኬ ሥራውን ለመጀመር ወደ አገሩ የተመለሰው በ1766 ዓ.ም. ነበር። ለአሥራ ሁለት ዓመታት ከአገሩ ተለይቶ በመቆየቱና የእናት አገሩን ቋንቋ በመጠኑም በመዘንጋቱ ሥራው ቀላል አልሆነለትም። ከቋንቋው ጋር እንደገና በደንብ እስኪላመድ ድረስ በአገልግሎቱ መጀመሪያ ላይ የሚናገረው በአስተርጓሚ ነበር።

ኩዋኬ፥ ቶምፕሰን የተባለው ሰው እንዳጋጠመው ሁሉ እርሱም የንግድ መለዋወጫ በሆነበት ስፍራ ላሉት ሰዎች ወንጌልን ለማስተማር ያደረገው ጥረት ከብዶት ነበር። እያንዳንዱ ሰው በክርስቶስ እንዲያምን የማድረጉ ተግባር ከባድ ነበር። ከዘጠኝ ዓመታት ሥራ በኋላ የተጠመቁት




አምሳ ሁለት ሰዎች ብቻ ነበሩ። ይህም አውሮፓውያንና ዲቃላዎቹን (ከነጭና ከጥቁር ዝርያ የሚወለዱትን) የሚጨምር ነበር። በሥራው ላይ የገጠመው አቢይ ችግር፥ በከፍተኛ ሥልጣን ላይ የነበሩትን ጨምሮ አውሮፓውያኑ የሚያሳዩት መጥፎ ምሳሌነት ነበር።

እንደ ብዙዎቹ መጋቢያን ሁሉ ቄስ ፊሊፕ ኩዋኬ ለብዙ ዓመታት በትጋት ሠርቶ እምብዛም መልካም ውጤቶችን ባለማየቱ ተስፋ ቆርጦ ነበር። ወንጌልን ለሌሎች ለማዳረስ በየስፍራው ለመንቀሳቀስ ቢሞክርም አልተሳካለትም። በ1790 ዓ.ም. ደግሞ ከመጋቢነት ይልቅ ንግድ ይበልጥ

ያጓጓው ይመስላል። በመሆኑም ከዚያ ወዲህ እስከ ዕለተ ሞቱ (1816 ዓ.ም.) ድረስ የመጋቢነትንና የሚስዮናዊነቱን ሥራ ያካሂድ የነበረው በትርፍ ጊዜው ሳይሆን አልቀረም።

ምንም እንኳን የቄስ ፊሊፕ ኩዋኪ የመጨረሻ የአገልግሎት ዘመኑ እንደ መጀመሪያዎቹ ዓመታት የተሳኩ ባይሆኑ፥ ምዕራብ አፍሪካ ውስጥ በአፍሪካውያን መካከል ይሠራ ዘንድ በእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን በመጋቢነት የተሾመ የመጀመሪያው አፍሪካዊ ነው። በመሆኑም፥ በአፍሪካ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጥናታችን ውስጥ ተገቢ ስፍራ የሚገባው ሰው ነው። በአካባቢው ጠረፎች የነበሩት አውሮፓውያን ለክርስትና እንዲህ ያለውን መጥፎ ስም ባያተርፉለት፥ ኖሮ የፊሊፕ ኩዋኪ የድካም ፍሬ ከዚህ እጅግ የላቀ ይሆን ነበር። እራሳቸውን "ክርስቲያን" ብለው የሚጠሩ፥ ነገር ግን እውነተኛ ክርስቲያን ያልሆኑ፥ ምግባረ ብልሹዎችና አኗኗራቸው የከፋ ሰዎች ለክርስቶስ ዓላማ ወይም ለወንጌሉ ከፍተኛ መሰናክሎች እንደሚሆኑ ይህ መልካም ማስገንዘቢያ ነው።

## ጥያቄዎች

1. የፕሮቴስታንት ሚስዮናውያን በመጀመሪያ ሥራቸውን የጀመሩባቸው ሁለት ሥፍራዎች የትኞቹ ናቸው?

2. በአሥራ ስምንተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ከሆቴንቶቶች ጋር የሠራው ጀርመናዊ ሚስዮናዊ ማን ነበር? ደቡብ አፍሪካን ትቶ የሄደው ለምን ነበር?

3. ስለ ቄስ ፊሊፕ ኩዋኪ ሕይወትና ሥራ በአጭሩ ይግለጡ።